# የ 1ኛና የ2ኛ ቆሮንቶስ

## የጥናት መምሪያና ማብራሪያ

በትምህርተ መለኮት ማስፋፊያ (ት.መ.ማ.) መልክ የተዘጋጀ

ጸሐፍ፡- በቄስ ኃይሉ መኮንን

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

ይህ የጥናት መምሪያ
የሚያተኩረው በቤተ ክርስቲያን
አገልግሎት ላይ በተሰማሩ
ሰዎች ላይ ሲሆን የጥናት
መምሪያውን በብዙ የተለያዩ
መንገዶች መጠቀም ይቻላል።
በግል የእግዚአብሔርን ቃል
ለማጥናትም ሆነ በአዋቂዎች
የሰንበት ትምህርት ቤት ወይም
በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት
ቤት መጠቀም ይቻላል።

ይሁንና መምሪያው የተዘጋጀው
በትምህርተ-መለኮት ማስፋፊያ
(ት.መ.ማ) መልክ ነው።
በመሆኑም ይህ መጽሐፍ
መምህርን ተከቶ ስለ መጽሐፍ
ቅዱስ ትምህርተ-መለኮት
ወይም አገልግሎት ለተማሪው
ጠቃሚ ትምህርቶችን
ያስተላልፋል። ተማሪው በዚህ
የጥናት መጽሐፍ እየተመራ
ጥያቄዎችን በመመለስና
የተማረውን ከሕይወቱ ጋር
በማዛመድ በቀን አንድ ሰዓት
ያህል ጊዜ ያሳልፋል።

ከሁሉም የላቀ ትርፍ
የሚገኘው ደግሞ ተማሪዎቹ
በሳምንት አንድ ቀን
ተሰባስበው የተማሩትን
ሲከልሱና የእግዚአብሔር ቃል
እንዴት ካሉበት ሁኔታ ጋር
እንደሚዛመድ ሲወያዩ ነው።

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያ እትም 1985 ዓ.ም (1993 A.D)
2ኛው እትም 1988 ዓ.ም (1995 A.D)
3ኛው እትም 1990 ዓ.ም( 1998 A.D)
4ኛው እትም 1994 ዓ.ም (2001 A.D)
5ኛው እትም 1995 ዓ.ም (2003 A.D)

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ. ቁጥር 127
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# 1ኛ ቆሮንቶስ እና 2ኛ ቆሮንቶስ

## አጠቃላይ መግቢያ

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ተልእኮ ትምህርት መጽሐፍ ውስጥ የምናጠናው በአዲስ ኪዳን የሚገኙትን የ1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ መልእክቶች ነው። ይህንን መጽሐፍ ስታጠና በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተፃፈውን ነገር በማስተዋል አንብበው። ለጥያቄዎቹም በጥንቃቄ አስበህ መልስ ስጥ። የእግዚአብሔርን ቃል በግልህ እንዴት አድርገህ ማጥናት እንደምትችል ማወቁ ጠቃሚ ነው። ይህንን ማወቅ የምንችለው የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረውን በጸንብ በማስተዋልና ጥያቄ በመጠየቅ ነው። ስለዚህ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያው ከመሄድህ በፊት ጥያቄዎችን መመለስህንና የተሰጠህን ክፍል በጸንብ ማጥናትህን እርግጠኛ ሁን። ስለ መልሶቹም በማሰብ በዚያ ክፍል ያገኘኸውን ትምህርት በሕይወትህ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ሞክር። የእግዚአብሔር ቃል የሚጠና ብቻ ሳይሆን ልንታዘዘውና ልንጠብቀውም የሚገባ ቃል ነው።

ሮሜ 15፡4 «በመጽናትና መጽሐፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና» ይላል።

ይህንን መጽሐፍ እንደ ማጥኚያ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን እንደ መጽሐፍ ቅዱስም ማብረሪያ ልንጠቀምበት እንችላለን። ምንጊዜም 1ኛና 2ኛቆሮ. ስታጠናም ሆነ ስታስተምር ይህንን መጽሐፍ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

የጥያቄዎቹን መልስ በተለየ ደብተር ላይ ጻፍ። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ከሌለህ ለጥናትህ ይረዳሃልና ለማግኘት ሞክር። ከዚህ ጥናት ጋር አብረህ ሌላ የ1ኛ እና የ2ኛ ቆሮንቶስ መልዕክቶችን የሚያብረሪ መጽሐፍ ብታጠና ይጠቅምሃል።

ትምህርቶቹ ለተማሪው በሚያመች መንገድ በአምስት የጥናት ቀናት የተከፋፈሉ ናቸው። የእንዱን ቀን ትምህርት አንዴ እንደተቀመጥክ እመጨረስ ሞክር።

ሐዋርያው ጳውሎስ 1ኛ እና 2ኛ ቆሮንቶስን የጻፈው በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ችግሮች መነሣታቸውን ስለተረዳ እነዚያን ችግሮች ለመፍታት ነበር። እነዚያ ችግሮች አሁንም በእኛ ዘመን እየተደጋገሙ ይነሣሉ። ስለዚህ እነዚህ መልእክቶች ለችግሮቻችን ሐዋርያዊ መፍትሔ ይሰጡናል። ለምሳሌ ስለክርስቲያኖች መከፋፈል÷ ስለ ክርስቲያን ነፃነት÷ ስለ ወንጌላውያን ደመወዝ÷ ስለ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ቦታ÷ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ወዘተ ...። እነዚህን ስለመሳሰሉት ነገሮች በሰፊው ጽፎአል። እንግዲህ እነዚህን መልእክቶች በትጋት እናጥና! የ1ኛ ቆሮንቶስ ጥናት በመጀመሪያዎቹ የዘጠኝ ሳምንት ጥናቶች ውስጥ ይገኛል። የ2ኛ ቆሮንቶስ ደግሞ በመጨረሻዎቹ ዘጠኝ ጥናቶች ውስጥ ይጠናቀቃል።

# የ1ኛ ቆሮንቶስ መጽሐፍ ጥናት

## ትምህርት 1

### የ1ኛ ቀን ጥናት

#### መግቢያ

1ኛ ቆሮንቶስ የተጻፈው በሐዋርያው ጳውሎስ ነው፤ (1ኛ ቆሮ.1:1)። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ሐዋርያው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከተማ ለአሥራ ስምንት ወር በተቀመጠበት ጊዜ ነበር፤ (የሐዋ.18:1-11) አንብብ። በዚህ በቆሮንቶስ ከተማ የተለያዩ የሕዝብ ዘሮች ይኖሩ ነበር። በቤተ ክርስቲያኑም ውስጥ እንዲሁ የተቀላቀሉ ወገኖች ይገኙ ነበር፤ ለምሳሌ አህዛብና አይሁዶች ነበሩ። ይህን ዓይነት የዘር ልዩነት በዘመናችንም በየቤተ ክርስቲያኑ እናገኛለን። ይህንን የዘር ልዩነት በዚያን ጊዜ የመከፋፈል ዝንባሌ እንዳደረገ አሁንም ያው ችግር ሊነሣ ይችላልና መፍትሔውን በጥንቃቄ ከቃሉ እንመልከት።

ጥያቄ 1. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ስለ ቆሮንቶስ ከተማና ቤተ ክርስቲያን አጀማመር የሚናገረውን አንብብ።

የቆሮንቶስ ሰዎች በንግድ በጣም የተራመዱ ስለነበሩ ሀብታሞች ነበሩ። ደግሞም የቆሮንቶስ ከተማ ሰዎች በኃጢአት በጣም የከፉ ከመሆናቸው የተነሣ «እንደ ቆሮንቶስ ሰው ኑር» የተሰኘ ምሳሌያዊ አነጋገርን አትርፈው ነበር። በዚህ ሕዝብ መካከል እግዚአብሔር ለራሱ ወገንን መረጠ፤ (1ኛቆሮ.6:9-11)። የኃጢአት ብዛት እግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያኑን ከመትከል አላገደውም!!

ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ የተነሣሣበት ሁለት ምክንያቶች ነበሩት:-

1ኛ/ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ደስ የማይል ሪፖርት ሰምቶ ስለነበር፤ (1:11፤ 5:1) ተመልከት።
2ኛ/ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ጳውሎስን የተለያዩ ጥያቄዎች ጠይቀውት ለጥያቄዎቻቸው መልስ ለመስጠት ነበር፤ (7:1፤ 16:17) ተመልከት።

ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከሰማቸው ሪፖርቶች ውስጥ አምስቱ የሚከተሉት ናቸው:-

- በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ መከፋፈል ነበር፤ (3:1-4)::
- ከአባሎቹ ውስጥ አንዱ በከፋ ዝሙት ይኖር ነበር፤ (5:1)::
- በአማኞች መካከል የፍርድ ቤት ክስ ይካሄድ ነበር፤ (6:6-8)::
- በክርስቲያን ነፃነት እያሳበቡ የሚፈጸሙ ስሕተቶች ነበሩ፤ (10:23-33)::
- በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ብዙ ከሥነ ሥርዓት ውጭ የሆኑ ድርጊቶች ነበሩ:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የጌታ እራት አፈጻፀም ሥርዓት ነበር፤ (11:17-30)::

የቆሮንቶስ ሰዎች ለጠየቁት ጥያቄዎች ሐዋርያው መልስ የሰጠባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው::

- ስለ ጋብቻ ጥያቄዎች፤ (ምዕራፍ 7)::
- ለጣዖት ስለተሠዋ ሥጋ፤ (10:14-22)::
- በጉባኤ ውስጥ ስለ ሴቶች መከናነብ፤ (11:1-16)::
- ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች (ከምዕራፍ 12-14)::
- ስለ ሙታን ትንሣኤ፤ (ምዕራፍ 15)::

ለእነዚህ ጥያቄዎች በሚሰጣቸው መልሶች በዚያን ጊዜ ስለነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ጠባዮች ብዙ ነገሮችን እንረዳለን:: በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን በሚገጥሟት ችግሮችና በዚያን ጊዜ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን በገጠሟት ችግሮች መካከል ብዙ መመሳሰል ስላለ ይህ መጽሐፍ ለእኛም አብያተ ክርስቲያናት ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎችን ይሰጣል:: በሚከተሉት ትምህርቶች ውስጥ እነዚህን ነጥቦች በዝርዝር እንመለከታቸዋለን::

ጥያቄ 2. ይህን ጸብጻቤ ለመጻፍ ያነሣሡት ሁለት ምክንያቶች ነበሩ፤ ለእያንዳንዱ ምክንያት የተሰጡትን ጥቅሶች በመመልከት ምክንያቶቹን ጥቀስ::

ጥያቄ 3. የሐዋ.18:1-11ን በጥንቃቄ በመመልከት የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ተርክ::

ጥያቄ 4. ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን የመሠረተው በስንተኛው የሚስዮናዊ ጉዞው ነበር?

ጥያቄ 5. በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ ችግሮች በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከነበሩት ችግሮች ጋር እንዴት ይመሳሰላሉ?

# ትምህርት 1

## የ2ኛ ቀን ጥናት

የ1ኛ ቆሮንቶስ የመጸብ ክፍፍል (አውትላይን እና ፈርስት ኮርንቲያንስ)

ጥያቄ 6. ከዚህ በታች የተሰጠውን የመጸብ ክፍፍል ከመመልከትህ በፊት 1ኛ ቆሮንቶስ መጽሐፍን በጥንቃቄ በመመልከት መጽሐፉን በመጸብ ከፋፍል (አውትላይን)። ከዚያ በኋላ ከዚህ በታች ከተሰጠው የመጸብ ክፍፍል ጋር አንተ ያወጣከውን የመጸብ ክፍፍል አስተያይ።

ምንም እንኳ በዚህ ጥናት ውስጥ ለአንድ ቀን የሚሆን ሐተታ ባይሰጥም 1ኛ ቆሮንቶስን በመጸብ መከፋፈል ብዙ ጥረትና ጊዜ የሚወስድ መሆኑን አስታውስ! በተቻለ መጠን ንባብህን በአንድ ጊዜ ለመፈጸም ሞክር።

1. ሰላምታ፤ (1:1-3)
2. ስለ ክርስቲያን ሕብረት፤ (ከምዕራፍ 1:4 እስከ ምዕራፍ 4)
3. ክርስቲያን በዓለም ውስጥ እንጂ ከዓለም አይደለም፤ (ምዕራፍ 5)
4. የምእመናን የእርስ በርስ መካሰስ፤ (6:1-11)
5. የአማኝ አካልና ዝሙት፤ (6:12-20)
6. ስለ ጋብቻ ምክር፤ (ምዕራፍ 7)
7. ጣዖትና ነጻነት፤ (ከምዕራፍ 8 እስከ ምዕራፍ 10)
8. በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ውስጥ የነበሩ ችግሮች፤ (ከምዕራፍ 11 እስከ ምዕራፍ 14)
   - የሴቶች መከናነብና አለመከናነብ፤ 11:1-16
   - ስለ ቅዱስ ቁርባን፤ 11:17-30
   - ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች፤ ምዕራፍ 12
   - የተሻለው መንገድ፤ ምዕራፍ 13
   - ስለ ልሳን ስጦታ መምሪያ፤ ምዕራፍ 14
9. ስለ ሙታን ትንሣኤ፤ (ምዕራፍ 15)
10. የመሰነባበቻ ሃሳቦች፤ (ምዕራፍ 16)

# ትምህርት 1

## የ3ኛ ቀን ጥናት

### ክፍል 1. ሰላምታ (1ኛቆሮ.1፡1-3)

### መግቢያ

ሐዋርያው ጳውሎስ ጸብጻቤ ለመጻፍ የተነሣሣው ችግሮች መነሣታቸው አስገድደውት ቢሆንም ጸብጻቤውን ሲጀምር ችግርን በመጥቀስ ሳይሆን የችግሬችን ሁሉ መፍትሔ የሆነውን የእግዚአብሔርን ጸጋ በመተረክ ነው። ይህን ለግል ክርስቲያን ኑሮአችንም ሆነ ለአገልግሎታችን መመሪያ ማድረግ አለብን። ችግር ሲያጋጥመን ማተኮር ያለብን ለችግሬችን መፍትሔ በሆነው በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ እንጂ በችግሬችን ትልቅነት ላይ መሆን የለበትም። ይህንን ክፍል ስናጠና የሐዋርያውን ምሳሌ እንከተል!

1ኛ ቆሮንቶስ 1፡1-3ን አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 7. «ሐዋርያ» ማለት ምን ማለት ነው? (የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመመልከት መልስህን አዘጋጅ፤ በተጨማሪም ኮሜንታሪ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ለመመልከት ሞክር፤ (ሉቃስ 6፡12-16፤ የሐዋ.1፡21-22፤ 1ኛቆሮ.9፡ 1-2፤ ገላ.1፡1-2)።

ጥያቄ 8. «በቆሮንቶስ ላለች ቤተ ክርስቲያን» ሲል የሚያመለክተው ወደ ሕንጻው ነው ወይስ ወደ ሕዝቡ? (ለመልስህ እንዲረዳህ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት፤ ሮሜ 16፡5፤ ፊልሞና 2)።

ጥያቄ 9. በቆሮንቶስ የነበሩ ክርስቲያኖች ብዙ መንፈሳዊ ድካሞች ሲገኙባቸው እንዴት ጳውሎስ «ቅዱሳን» ወይም «በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት» ይላቸዋል? (ለመልስህ ሃሳብ ከ1ኛቆሮ. 6፡9-11 ላይ ተመልከት)።

ጥያቄ 10. 1ኛቆሮ.1፡3ን ከሌሎች የጳውሎስ መልእክት መክፈቻዎች ሰላምታ ጋር አወዳድር። ያገኘኸውንም ውጤት በጽሑፍ አስፍር።

ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቱን ሲከፍት ሐዋርያነቱን በመናገር ይከፍታል። ይህም ገና ሲጀምር ጸብጻቤው የግል ሳይሆን በሐዋርያነት ጸረጃ የጻፈላቸው መሆኑን ያስረዳቸዋል። የሐዋርያን መመሪያ አለመቀበል የአንድ ተራ ሰውን

መመሪያ አለመቀበል አይደለም። የሐዋርያ ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነበርና! (1ኛቆሮ.14:37)። አንድ ሰው ሐዋርያ ሊባል የሚችለው በኢየሱስ ለሐዋርያነት ሲመረጥና ከሞት የተነሣውን ኢየሱስን በዓይኑ ካየ ነው። ኢየሱስ ካረገ በኋላ ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩ።

«በቆሮንቶስ ያለች የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን» ሲል በጳውሎስና በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች መካከል እግዚአብሔር ያለ መሆኑን ያስገነዝባል። የእግዚአብሔር መሆናቸው በ3:9 ላይና በ3:16 ላይ በሰፊው ተገልጿል። እነዚህን ጥቅሶች ተመልከታቸው። ቤተ ክርስቲያን በእጅ የተሠራ ሕንፃ ሳይሆን እግዚአብሔር ያዳናቸውና ከኃጢአት ያነፃቸው የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ሕዝቦችን ያመለክታል።

«በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት» ክርስቲያን ማለት በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የታጠበና የተቀደሰ ነው። በ1ኛ ጴጥ.1:1 እና 2 ላይ በክርስቶስ ደምና በመንፈስ ቅዱስ የተቀደስን መሆናችንን ያስረዳል። በኤፌሶን 5:25-27 ላይ ደግሞ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስና በቃሉ የተቀደሰ እንደሆነ ተጽፏል።

ጥያቄ 11. ክርስቶስን እንደ ግል መድኃኒት አድርገህ ተቀብለህ የተቀደስከው መቼ ነበረ? በየዕለቱስ ቅድስናህን የምታሳየው እንዴት ነው?

ክርስቲያን ገና ዕለት በዕለት ከሚሠራቸው ኃጢአቶች ነፃ ያልሆነ ሲሆን እንዴት ቅዱስ ሊባል ይችላል? መልሱ ይህ ቅድስና በእግዚአብሔር ፊት ያለውን አቋማችንን የሚገልጽ እንጂ በሥራችን ሙሉ ቅድስናን ያልተቀዳጀን መሆናችንን አይክድም። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በዕለት ኑሮአቸው ብዙ መንፈሳዊ ጉድለቶች ሲታዩባቸው በእግዚአብሔር ፊት ግን ፍጹም ቅዱሳን ነበሩ፤ (6:11ን በጥንቃቄ ተመልከት)።

«የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየሥፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር» ይህ ዐረፍተ ነገር ሁለት ሐሳቦችን በአንድ ጊዜ ያሳስበናል፡-

1ኛ. ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ የተስፋፋች እንጂ በአንድ ቦታ ብቻ የምትገኝ አለመሆንዋን ሲያስረዳ፤
2ኛ. እውነተኛ ምእመናን ደግሞ በየሥፍራው እርስ በርስ የሚሰበሰቡ መሆናቸውን ያስረዳል።

«ጸጋና ሰላም» በዘመኑ ይሰጥ የነበረ የሰላምታ ቃል ሲሆን ጳውሎስ ሐሳቡን ወደ ክርስቲያን ለውጦ «ጸጋና ሰላም» ከእግዚአብሔር የሚሰጡ በረከቶች መሆናቸውን ያስተምረል።

## ክፍል 2. ስለ ክርስቲያን ሕብረት (ከምዕ.1:4 እስከ ምዕ.4:21)

### * ሀ. መለያየት በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፤ 1:4-17::

1ኛ ቆሮንቶስ 1:4-17ን በጥንቃቄ በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ::

ጥያቄ 12. ጳውሎስ «ለክርስቶስ መመስከሬ በእናንተ ዘንድ እንጸናና» ሲል ምን ማለቱ ነው?

ጥያቄ 13. አገልጋይ ስለሚያገለግለው ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ለምን ማመስገን ይገባዋል?

ጥያቄ 14. በቁጥር 9 ላይ ሐዋርያው ክርስቲያኖች ስለ አንድ ነገር እርግጠኛ እንዲሆኑ ይነግረቸዋል፤ ያ ነገር ምንድነው?

ጥያቄ 15. በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመለያየት መነሻ የሆናቸው ምን ነበር? (ቁጥር 12ን ተመልከት::)

ጥያቄ 16. በውኃ ጥምቀትና በወንጌል መስበክ መካከል ያለውን ልዩነት በማጤን በአጭሩ መግለጫ ስጥ::

ጥያቄ 17. ሰዎች በውኃ ጥምቀት የሚመኩት ስለ ወንጌል ያላቸው አቋም ምን ስለሆነ ነው?

ምንም እንኳ የቆሮንቶስ ምእመናን በድካማቸው ሐዋርያውን ቢያደክሙትም በመጀመሪያ የሰበከላቸው ወንጌል በእነርሱ ዘንድ ሥር ሰዶ መገኘቱ እግዚአብሔርን ስለ እነርሱ እንዲያመሰግን ረድቶታል፤ «ለክርስቶስ መመስከሬ በእናንተ ዘንድ እንጸናና» ይላልና:: ይህ ጽናትም በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተመስክሮአል፤ «በነገር ሁሉ በቃልም በእርሱ ባለጠጎች እንድትሆኑ ተጸርጋችኋል»::

ጥያቄ 18. በሕይወትህ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የተገለፁት በምን መልኩ ነው? በምሳሌ ግለጽ::

በክርስቶስ ጸንተው እስከቆዩ ድረስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እየበዛላቸው እንጂ እያነሰባቸው አይሄድም፤ «የጌታችንን መምጣት ስትጠባበቁ አንድ የጸጋ ስጦታ እንኳ አይጐድልባችሁም»:: የጌታን መምጣት መጠባበቅ ማለትም በክርስትና ሕይወት ታማኝ ሆኖ መኖር ማለት ነው:: ይህ በክርስትና ሕይወት ታማኝ ሆኖ መኖር ራሱ በጸጋው የሚሰጠን እንጂ በራሳችን ጥረት የምናሳየው አይደለም፤ «<u>እርሱም</u> ያለ ነቀፋ እንድትሆኑ እስከፍጻሜ ድረስ ያጸናችኋል»:: በሚገጥሙን ነገሮች ሁሉ ታማኝ ሆነን ስንገኝ በነገር ሁሉ እግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ እንደሚረዳን እርግጠኞች መሆን እንችላለን::

ይህ ጽናት የሚመጣው:- 1ኛ. አገልጋዮች በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ተገልጋዮችን ሲረዱ፤ 2ኛ. ተገልጋዮች የተነገረቸውን ጉድለት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሲያርሙ ነው:: ይህንንም አገልግሎት ሐዋርያው በ1:10-13 ባለው ውስጥ ያቀርብላቸዋል:: እንግዲህ እንደ ተስፋ ቃሉ መሠረት እስከፍጻሜ ጸንተው ለመቆየት ይህን የማይገባ መከፋፈላቸውን ማረም ይኖርባቸዋል::

ሐዋርያው «ለማጥመቅ ክርስቶስ አልላከኝምና ወንጌልን ልሰብክ እንጂ» ሲል ጥምቀትና ወንጌል የተለያዩ መሆናቸውን ያሳያል:: ጥምቀት ምልክት ብቻ እንጂ የደህንነት ኃይል የለውም:: ወንጌል ግን ፍጹም የደህንነት ኃይል ነው፤ (ሮሜ 1:16 እና 17 ተመልከት):: ስለዚህ ጥምቀት የማዳን ኃይል ይሰጣል ብለው የሚያምኑ በዚህ ሐዋርያዊ ቃል ሃሳባቸውን ማረም ይገባቸዋል::

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለያየትን የፈጠረው ክርስቲያኖቹ ዓይናቸውን ከክርስቶስ ላይ አንሥተው በሰው ወይም ሰው ሰራሽ በሆኑ ሥጋውያን ሥርዓቶች መደገፍ ስለጀመሩ ነው:: ይህም በክርስቶስ ላይ ሳይሆን በአገልጋዮቻቸው ላይ መደገፍና እንዲሁም በወንጌል ቃል ሳይሆን በጥምቀት መመካት ነው::

የጳውሎስ ምኞት የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በአንድ መንፈስና በአንድ ልብ እንድትዋሃድ ነበር:: እነርሱ ግን እውነተኛ ደህንነት በሚገኝበት በመስቀሉና በኢየሱስ ላይ ዓይናቸውን ከማድረግ ፋንታ በሰዎች ላይ ነበር የታመኑት:: በተጨማሪም አንዳንዶች የአይሁድ ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆነው የኬፋ (ለጴጥሮስ የተሰጠ ሌላ ስም) ተከታይ ነኝ እያሉ÷ ሌሎች ደግሞ የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆነው የጳውሎስ ተከታይ ነኝ እያሉ÷ በመጨረሻም ደግሞ ሌሎች ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን መሥርቶ ከሄደ በኋላ እዚያ ድረስ መጥቶ የሰበከውና ያስተማረው የአጵሎስ ተከታይ ነን በማለት እርስ በርሳቸው ተከፋፍለው ነበር:: (የሐዋ.18:24-19:1 ተመልከት):: ከዚህም በላይ አንዳንዶች ከትዕቢት የተነሣ የእኛ ከሌሎች ይሻላል በማለት ራሳቸውን «እውነተኞቹ የክርስቶስ ተከታዮች» በማለት ሰይመዋል::

አማኞች በሙሉ እምነታቸው የተመሠረተው በኢየሱስ ክርስቶስና በመስቀሉ ላይ ነው:: ደህንነታቸውንም የሚያገኙት ለኃጢአታቸው በሞተው በክርስቶስ በማመን ነው:: ይኸኔ ምንም መከፋፈል በሌለበት በክርስቶስ ቤተሰብ ውስጥ ይጠመቃሉ:: ስለዚህም መከፋፈልና መደባደብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ቦታ አይኖረውም:: ምንም እንኳ የተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት በተለያዩ ሃሳብ ቢመሩም÷ እምነታችን በዚህ ላይ አይደለም:: እምነታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እስከሆነና የእርሱን ቃል በታዛዥነት እስከጠበቅን ድረስ የተለያዩ ሃሳብም ቢኖረን እንኳን አብረን ልናመልክ እንችላለን::

ጥያቄ 19. ሀ/ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ላለው መከፋፈል ዋነኛው ምክንያት ምንድነው?

ለ/ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ችግር ጋር አነፃፅረው። መፍትሔውስ ምንድነው?

* ለ. የዓለም ጥበብና የእግዚአብሔር ጥበብ፤ (1:18-31)

(1ኛ ቆሮንቶስ 1:18-31ን) አንብብ።

ጥያቄ 20. የመስቀሉ ቃል ሞኝነት ነው ሲል እንዴት የእግዚአብሔር ነገር ሞኝነት ሊሆን እንደቻለ አስረዳ።

ጥያቄ 21. እግዚአብሔር ራሱ የሰውን አእምሮ የፈጠረ ሲሆን ለምን የሰውን ጥበብ መልሶ ይቃወማል?

ጥያቄ 22. ለአይሁድና ለግሪኮች ለእያንዳንዳቸው የወንጌሉ ቃል እንዴት መሰናከል ሊሆን ቻለ? በራስህ ሕይወት ይህን መሳይ ሰዎች አጋጥመውህ ከሆነ በጽሑፍ አስፍር።

ጥያቄ 23. እግዚአብሔር የዓለምን ጥበብ ለመቃወም ሁለት እርምጃዎችን ወሰደ፤ እነዚህ እርምጃዎች ምንና ምን ናቸው? (ለዚህ ጥያቄ መልስ በተለይ ቁጥር 18ና 26ን ተመልከት)።

የመስቀሉ ቃል ሞኝነት የሆነው በራሱ በእውነትም ሞኝነት ሆኖ ሳይሆን በዓለማውያን ዘንድ ሞኝነት ሆኖ ተቆጠረ ማለት ነው። አናጺዎች የጣሉት ድንጋይ የማዕዘን ራስ ሆነ ከሚለው ቃል ጋረ አብሮ የሚሄድ ቃል ነው። «ለሚጠፉት ሞኝነት ነው ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው»። ዓለማመን የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይል ወደ ሞኝነት ቀየረባቸው። ግን ይህ የናቁት «ሞኝ» ነገር አንድ ቀን በፍርድ ያፋጥጣቸዋል፤ (የሐዋ.17: 30-31፤ ሮሜ 2:16፤ ራዕይ 6:16ና 17)።

እግዚአብሔር የሰውን ጥበብ ቢፈጥርም ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን ጥበብ አዙሮ እግዚአብሔርን መዋጊያ ስላደረገው እግዚአብሔር የሰውን ጥበብ ከንቱ እንዲሆን አድርጓል። ይህች ዓለም ሞኝ በምትለውና በምትንቀው በመስቀል ቃል የደህንነትን መንገድ በማቅረብ ነው። ስለዚህ የዓለም መርማሪም ሆነ ተራ ያልተማረው ራሱን ከንቱ አድርጎ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አለበት፤ (ቁጥር 21)።

እግዚአብሔር የዓለምን ጥበብ በሁለት መንገድ ከንቱ አደረገ፤ ሞኝነት በተባለው በመስቀል በኩል ደህንነትን ማዘጋጀቱና የዓለምን ተራ ሰዎች የመንግሥቱ ወራሾች አድርጎ መምረጡ ነው። የዓለም ተራ ነገር የተመረጠበት ምክንያት ያ ተራው ነገር እውነትም ከከበረው ነገር ተመራጭ ሆኖ ስለተገኘ ሳይሆን በራሱ የሚመካበት ስለሌለውና ባዶነቱን በቶሎ ስለሚገነዘብ ብቻ

ነው:: «የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ» የተባለው ቃል የሰው ሁሉ መመሪያ መሆን ይገባዋል፤ ነገር ግን የዓለም አዋቂዎች በጥበባቸው እየተመኩ በመስቀሉ ቃል ይሰናከላሉ፤ (ቁጥር 25-31 ተመልከት):: ስለዚህ መስቀሉ ጥበበኞችን በትዕቢታቸው ስላጠመዳቸው ሞኝነት መሆኑ ቀርቶ ሰው በጥበቡ ሊደርስበት የማይችል ረቂቅ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው፤ (ቁጥር 24):: ይህን ሀሳብ ሐዋርያው በአጉሮ አነጋገር ሲገልጸው እንዲህ ይላል፤ «ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና»:: ይህ ማለት ከሰው ጥበብ ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት የበለጠ ጥበብን ያሳያል::

የእግዚአብሔር ጥበብ የተገለጸው የእግዚአብሔር ጥበብ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል የተገለጸው በኢየሱስ ምጽዓትና ሞት ነው:: ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም ምድር ላይ መጥቶ የኖረው በታላቅ ኃይልና ክብር አልነበረም:: እንዲያውም እንደ አገልጋይ ሆኖ ነበር የመጣው:: የመጣውም ለኃጢአታችን ሲል ለመሞትና በዚህም ሞቱ የደህንነትን መንገድ እንዲከፍትልን ነበር:: ላልዳኑት ይህ የደህንነት መንገድ ሞኝነት ነው:: አይሁዳውያን ይጠብቁ የነበረው ከጠላቶቻቸው እጅ ነፃ የሚያወጣቸውን ታላቅና ድል አድራጊ ንጉሥ ነበር:: እንደማንኛውም ተራ ነፍሰ ገዳይ የሚሰቀል መሢህ አልነበረም የሚጠብቁት:: አሕዛቦችም፥ በተለይ ግሪኮች ታላቁን የእግዚአብሔር የደህንነት ዓላማ ሊረዱ አልቻሉም:: ነገር ግን የድል ምልክት የሆነው መስቀል በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ ዋነኛውን ሥፍራ ይዟል:: በዚህ መስቀል አማካኝነት:-

ሀ. ሰይጣን ተሸንፏል::
ለ. በቅዱሱ እግዚአብሔርና በኃጢአተኛው ሰው መካከል የእርቅ መንገድ ተከፍቷል::
ሐ. እንደ እግዚአብሔር ልጆች የቅድስናና የጽድቅ ኑሮ እንድንኖር ኃይሉ ተሰጥቶናል::

የእግዚአብሔር ዓላማና ጥበብ ከሰው የተለየ መሆኑን የምናረጋግጠው፥ እግዚአብሔር በዓለም የተናቀውን ነገር ወደ ራሱ አምጥቶ ለክብሩ ሲጠቀምበት በማየታችን ነው:: ድሃውን፥ ያልተማረውንና ደካማውን እግዚአብሔር ጥበበኛና ኃይለኞች ነን የሚሉትን ለማደናገር ሲል ይጠቀምበታል::

ጥያቄ 24. ሀ/ ይህንን ከላይ የተጠቀሰውን የእግዚአብሔርን ጥበብ የመናቅን ጉዳይ ለሰዎች በምትመሰክርበት ጊዜ በምን መልኩ ነው ያየከው?

ለ/ እግዚአብሔር በዓለም ዓይን የተናቀውን ሰው መርጦ በታላቅ ኃይል ለእርሱ አገልግሎት ሲያዘጋጀው ያየከው ሰው ካለ እንዴት አድርጎ ይህንን ሰው ተጠቀመበት?

## ትምህርት 1

## የ4ኛ ቀን ጥናት

* ሐ. አገልግሎት በሰው ጥበብ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጥበብ መሆን አለበት፤ (1ኛቆሮንቶስ ምዕራፍ 2)

### መግቢያ

እግዚአብሔር በጠቢባን ሳይሆን በጸካሞች ይጠቀማል ሲባል ያገኘነውን እውቀት እግዚአብሔር አገልግሎት ላይ አናውለው ማለት አይደለም፤ ወይም ደግሞ ለእግዚአብሔር አገልግሎት በቂ ዝግጅትና ትጋት አናሳይ ማለት አይደለም። ግን ሁሉንም ካደረግን በኋላ መንፈስ ቅዱስ ካልተጠቀመበት የእኛ ጥረት ብቻውን ከንቱ መሆኑን መገንዘብ ማለት ነው።

1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 2ን አንብብ።

ጥያቄ 25. የሐዋርያው ስብከት «መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበር» ይህ ሊሆን የቻለው ጳውሎስ ማንን ስለሰበከ ነው?

ጥያቄ 26. በቁጥር 7 ላይ «ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር እንናገረለን» ሲል ምን ማለቱ ነው?

ጥያቄ 27. አማኞች ስውር የሆነውን የእግዚአብሔርን ጥበብ እንዴት ሊያውቁት ቻሉ?

ሐዋርያው ወንጌልን በቃልና በጥበብ ብልጫ አልሰበከም፤ ይህም ማለት ወንጌልን ለቆሮንቶስ ሰዎች በሰበከ ጊዜ የቆሮንቶስ ሰዎች በሚያደንቁት በግሪኮች ፍልስፍናና የንግግር ዘይቤ (ርሂቶሪክ) በመጠቀም አልነበረም። ነገር ግን አዋቂ ነን የሚሉ በሚንቁት በክርስቶስ ወንጌል ተመክቶ ነበር። በዚያም አላፈረም፤ የእግዚአብሔር የማዳን ኃይል በወንጌል በኩል ተገልጿልና፤ (ሮሜ 1፡16ና 17)።

ይህን ነጥብ በደንብ ልንገነዘበው ይገባናል። በማያምኑ ሰዎች ፊት የክርስትናን እምነት ተቀባይነት ለማስገኘት ብለን ወንጌልን በተለያየ የሳይንስና የፍልስፍና ቅመም ብናጅለው እናበላሸዋለን። ለዓለማውያን እንዲዋጥላቸው እናደርግ ይሆናል፤ ግን ወንጌልን ሳይሆን የሰውን ጥበብ የእምነታቸው መሠረት አደረግን ማለት ነው። ጳውሎስም የፈራው ይህንኑ ነበር፤ (ቁጥር 4 እና 5)

ጥያቄ 28. አንዳንድ ሰዎች ወንጌልን ለውጠው በሰው ጥበብ ሲሰብኩ ያየህበት ጊዜ አለ? ካየህ ወንጌሉን የለወጡት እንዴት ነበር?

«በበሰሉት መካከል ጥበብን እንናገረለን» (ቁጥር 6)። የበሰሉት ማለቱ በመንፈስ ቅዱስ አስተማሪነት የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር የተረዱትን ማለቱ ነው። የእግዚአብሔር ጥልቅ ነገር የመስቀሉ ቃል ነው። ያልበሰሉት ሥጋውያን ወይም ዓለማውያን ይህንን ነገር ሊገነዘቡት አይችሉም። «ያልበሰሉት» የተባሉት በመንፈስ ያላደጉ ክርስቲያኖች ሳይሆኑ ፍጹም ወንጌልን ያልተቀበሉትን ዓለማውያን ነው። ይህ ለመሆኑ ማስረጃው ቁጥር 14-16 ነው።

ወንጌል «እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብረችን የወሰነውን ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር» ይገልጣል፤ (ቁጥር 7)። በምስጢር መገለጥ ማለትም ሰው በሚሰጠው መመረመር የተገኘ ሳይሆን እግዚአብሔር የገለጠው ብቻ ነው ማለት ነው። ይህ እውቀት የሳይንስ እውቀት አይደለም፤ ምክንያቱም ለተመረመረና ላጠና ሁሉ የሳይንስ ጥበብ ክፍት ነው፤ ይህ ግን ክፍትነቱ እግዚአብሔር ለገለጠላቸው ብቻ ነው።

ይህ የወንጌል ምስጢር ከጊዜ በኋላ የታሰበ ትኩስ ነገር አይደለም፤ አስቀድሞ ከዘመናት በፊት በእግዚአብሔር ታስቦ ነበር። ደግሞም ይህ በእግዚአብሔር ብቻ እንጂ ከሰዎች በማንም አእምሮ ውስጥ ያደረ አልነበረም፤ (ቁጥር 9)።

እኛ ማለት አማኞች ይህን ምስጢር እንዴት ልናውቀው ቻልን? «ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው»፤ (ቁጥር 10)። ይህም ለእኛ የተሰጠበት ምክንያት በእኛ ውስጥ ሊያሰጠን የሚችል ነገር ተገኝቶብን ሳይሆን «እንዲያው» ነው የተሰጠን፤ (ቁጥር 12)። ስለዚህ ወንጌልን የምናምነውም የምናስተምረውም በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት ብቻ መሆኑን መገንዘብ አለብን። በወንጌል ላይ የሰውን ጥበብ በማንኛውም ደረጃ ላይ ከጨመርንበት እንበርዘዋለን።

ነገር ግን ለእኛ የእግዚአብሔር ጥበብ የተገለጸልን የት ነው? የተገለጸው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው። በቃሉ ውስጥ የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ጥበብ መንፈስ ቅዱስ ይወስድና ለእኛ እንደሚገባን አድርጎ በምንገኝበት ሁኔታ ውስጥ ተግባረዊነቱን ይገልጽልናል። ትምህርታችንና አመለካከታችን በደበልጥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በተደገፈ ቁጥር መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ቃሉን እንደ ጥበብ በእኛና በሌሎች ሕይወት ውስጥ እንድንጠቀምበት ያደርገናል።

ጥያቄ 29. ላልዳኑት ግልፅ ያልሆነውን ነገር መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን

ቃል በመጠቀም እንዴት አጽርጎ ነው ገልፀ ያጸረገልህ?

እኛ እንዲህ የምናጸንቀው ወንጌል ለማያምኑት ምኝነት የሆነበት ምክንያት ምስጢሩ ሳይገባቸው ስለቀረ ነው፤ (ቁጥር 14-15)። ወንጌል ቀርቶ በወንጌል የሚያምኑት ራሳቸው ለማያምን ሰው አስተሳሰባቸው አይገባውም፤ ስለዚህ የማያምኑት አማኞችን በከንቱ ሲቃወሚቸውና በጽንቁርና ተመርኩዘው እምነታቸውንና ለሕይወታቸው ስንት ስያሜና ስጽብ ሲሰጡ ይታያሉ። ክርስቶስን የማያውቅ የአማኝንም አስተሳሰብ ሊያውቀው አይችልም፤ (ቁጥር 16)።

## ትምህርት 1

### የ5ኛ ቀን ጥናት

በዚህ ሳምንት ጥናት ላይ ክለሳ አጽርገህ የመወያያ ጥያቄዎችንም በጥናት መልክ ሠርተህ ከጨረስክ በኋላ ራስህን ለሳምንታዊው ስብሰባ አዘጋጅ።

### ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ:- ከተማሪዎቹ ጋር ሊካፈለው የሚችል በዚህ ሳምንት የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚገኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወይም ሃሳብ በመምረጥ የስብሰባው መሪ ከ5 እስከ 10 ደቂቃ ያህል ጊዜ የሚወስድ የስብከት ጊዜ ማዘጋጀት አለበት።

2. ጸሎት:- አብረቻሁ ለ10 ደቂቃ ያህል ስለእያንዳንዳቸሁና ስለ ቤተ ክርስቲያን ችግር ጸልዩ።

3. ክለሳ:- ለ15 ደቂቃ ያህል የዚህን ሳምንት ትምህርት ጠቅለል ባለ መልኩ ተመልከቱት (ክለሳ አጽርጉ)።
መምህር:- እያንዳንዱ ተማሪ ሳምንታዊ ትምህርቱን ማጠናቀቁንና በጽንብ መረዳቱን ይዩ። እያንዳንዱ ተማሪ ከትምህርቱ የተማረውን ነገር በዝርዝር ይጻፍ።
የስብሰባው መሪ:- በዚህ ሳምንት የትምህርት ክፍል ላይ የተመሠረተ ትንሽ ፈተና ብትሰጣቸው ይመረጣል።

4. ውይይት:- ለ25 ደቂቃ ያህል የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው። ሁሉም ሰው የራሱን ሃሳብ ማካፈሉን እርገጠኛ ሁን።

የእነዚህን ጥያቄዎች ተግባራዊነት በማሳየት ተማሪዎቹ ሰፋ ያለ አመለካከት እንዲኖራቸው አድርግ።

5. ጸሎት፡- የተማራችሁትን ነገር ተግባራዊ እንድታደርጉት የእግዚአብሔርን እርዳታ በጸሎት በመጠየቅ ስብሰባችሁን ዝጉ።

1/ ሀ. ሐዋርያው በዚህ ጰብጸቢው ላይ የዓለምን ጥበብና የእግዚአብሔርን ጥበብ ያነፃፀረበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?
ለ. እንዴት ነው እኛ ክርስቲያኖች አንዳንዴ በእግዚአብሔር ጥበብ ላይ ከመደገፍ ይልቅ በዚህ ዓለም ጥበብ ላይ የምንተማመነው?

2/ ሀ. በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለያየት በመፈጠሩና በዓለም ጥበብ መመካት መካከል ያለው ግንኙነት ምንድነው?
ለ. እንዴት ነው ይህ ችግር ዛሬ በቤተ ክርስቲያንህ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚታየው?

3/ የእግዚአብሔርን መናር ከማያምኑት ጋር በመከራከር ብቻ ለማሳመን መሞከር ተገቢ ያልሆነበት ምክንያት ምን እንደሆነ አስረዳ።

4/ በመስቀሉ በኩል የእግዚአብሔር ጥበብ እንዴት ሊገለጥ ቻለ?

5/ ሀ. የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስን የጠየቁት ጥያቄዎች ምን ምን ነበሩ?
ለ. በአንተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚጠየቁት ጥያቄዎች ጋር እነዚህ ጥያቄዎች የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

## ትምህርት 2

### የ1ኛ ቀን ጥናት

### መ. መንፈሳዊ ጉልምስና (1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 3)

#### መግቢያ

1ኛቆሮንቶስ ምዕራፍ 3 ስለ መንፈሳዊ ጉልምስና በሰፊው ያስተምራል። በመንፈስ የማደግ ዋናው ምልክት ክርስቲያን ሕይወቱን ለእግዚአብሔር አገልግሎት መስጠቱ ነው። በቁጥር 9 ላይ «ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና» ይላል። ክርስቲያን እግዚአብሔርን ለማገልገል

ታጥቆ ሲነሣ ከእርሱ ጋር አብሮት የሚሠራው እግዚአብሔር እንደሆነ ተረድቶ በእምነት መሠማረት አለበት። እኛም የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆናችንን ብቻ ሳይሆን በአገልግሎታችን ተባባሪ ሆኖ ኃይል የሚሰጠን እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን መገንዘብ አለብን።

1ኛ ቆሮንቶስ 3ን አንብብ።

ጥያቄ 1. ከቁጥር 1-4 ያለውን ክፍል በጥንቃቄ ተመልከተህ በሥጋዊነትና በዓለማዊነት መካከል ያለውን መወረረስ አስረዳ።

ጥያቄ 2. ከቁጥር 5-9 ባለው ክፍል ውስጥ ሁለት ሠረተኞች ተጠቀሰዋል፤ እነማን ናቸው?

ጥያቄ 3. ቁጥር 10-15ን በመመልከት «የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጐዳበታል፤ እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደ ሚድን ይሆናል» የሚለውን በራስህ አማርኛ በአጭሩ ገልጸህ አስረዳ።

ጥያቄ 4. ቁጥር 15ንና 1ኛቆሮንቶስ 6፡9ና 10ን አስተያይተህ በሁለቱ መካከል ያለውን ተቃራኒ አነጋገር አስታርቅ።

## መንፈሳዊ ጉልምስና የሚከተሉትን ያሳያል

1ኛ. ሥጋዊነትን ያስወግዳል፤ (1-4)

2ኛ. አገልግሎት ምን እንደሆነ ይገነዘባል፤ (5-9)

3ኛ. የአገልግሎቱን ድካም በእግዚአብሔር ሚዛን ላይ ያስቀምጣል፤ (10-17)

4ኛ. በሰው ጥበብ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጥበብ ያገለግላል፤ (18-23)

ከላይ ከ1-4 የተዘረዘሩትን ነጥቦች በየተራ እንመልከታቸው።

## 1ኛ. መንፈሳዊ ጉልምስና ሥጋዊነትን ያስወግዳል (1-4)

በመሠረቱ ሕፃንነት አስነቃፊ አይደለም፤ ነገር ግን ሰው በሕፃንነት ሲሰነብት የጤንነት አለመሆኑ ገልጽ ነው። በመንፈሳዊ ደረጃ ነገሩ የከፋ ነው። በመንፈሳዊ ሕይወቱ የማያድግ ክርስቲያን ባለበት አይቆምም፤ ወደ ኋላ በማፈግፈግ ወደ ሥጋዊነት እያዘነበለ ይመጣል። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ጽኑ ምግብ በመመገቢያቸው ወቅት ወተት መጋት ነበረባቸው። ይህ ሕፃንነት ግን ኃጢአትንም አስከተለ፤ «ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም። ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደለምን?» (ቁጥር 2ና 3)።

በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በኩል ሥጋዊነታቸው የተገለጠው እርስ በርስ ባለመስማማት ነበር፤ በእኛስ በኩል ሥጋዊነታችን በምን ይገለጣል? አለመጎልመስ እስካለ ድረስ ሥጋዊነትም አብሮ እንዳለ መገንዘብ አለብን:: ግን የሥጋዊነት መግለጫ ሊለያይ ይችላል:: መለያየትና መከረከር አለመቀረረብ÷ ለመንፈሳዊ ነገር ቅድሚያ አለመስጠት÷ ግድየለሽነት የመሳሰሉት የሥጋዊነት መግለጫዎች ናቸው::

ጥያቄ 5. ሀ/ በሕይወትህ መንፈሳዊ ጎልማሳ ነህ? መሆንህን ወይስ አለመሆንህን በምን አወቅህ?
ለ/ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ብዙ ሰዎች መንፈሳዊ ሕፃናት ናቸውን? አለመጎልመሣቸውን በምን ያሳያሉ?

## 2ኛ. መንፈሳዊ ጉልምስና አገልግሎት ምን እንደሆነ ይገነዘባል፤ (5-9)

ሥጋውያን ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ከመለያየታቸውም በላይ በአገልጋዮች መካከልም የመለያያ ምክንያት ይሆናሉ፤ (ለምሳሌ ያህል ማርቆስ በጳውሎስና በባርናባስ መካከል መለያየትን ፈጠረ፤ የሐዋ.15:36-41):: ይህንም የሚያደርጉት የአገልግሎት ነገር ገና ስላልገባቸው ነው፤ (ቁጥር 6-8)::

ሰው የእግዚአብሔር መሆኑን ከተገነዘበ «የእከሌ ተከታይ ነኝ» ከሚለው የሕፃን ጭቅጭቅ ውስጥ አይገባም:: የእግዚአብሔር ከሆነ አገልጋዮቹ በሙሉ የርሱ ናቸው እንጂ አንዱ ወይም ሁለቱ ብቻ አይደሉም::

የእግዚአብሔር ሀብት መሆናችሁን የተገነዘባችሁ ስንቶች ናችሁ? የእግዚአብሔር ከሆናችሁ በሕይወታችሁ እግዚአብሔርን ለማስቀደም ምን ያህል ጥረት ይታይባችኋል? ለምትወስኑት ውሣኔ «ይህ እግዚአብሔርን በበለጠ እንዳገለግል ይረዳኛል» ብላችሁ ከረሳችሁ ጋር ትነጋገረላችሁ ወይ? ወይስ እንዳ ከሃዲ የእግዚአብሔር ነገር ከውሣኔአችሁ ውስጥ አይገባም? ለአንዳንድ ክርስቲያን ነን ባዮች በእግዚአብሔር ማመን እንዳ ጌጥ ትርፍ ነገር እንጂ የሕይወታቸው መነሻና መድረሻ አይደለም:: «የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ» የሚለው ቃል በሕይወታቸው ውስጥ ቦታ ያለው አይመስልም:: እንግዲያስ አንድ ሰው ይህን ካልተገነዘበ የመንፈሳዊ አገልግሎት ትርጉሙ በፍጹም ገና አልገባውም:: ይህም ከሆነ መንፈሳዊ ሕፃንነቱ ሥር ከመስደዱ የተነሣ አስተሳሰቡ ዓለማዊ ነው::

በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ እግዚአብሔር ለተለያየ ሥራ የተለያየ መሪዎችን ነው ይጠቀማል:: እንዳ ጳውሎስ ያሉ ወንጌላውያን ወንጌልን ለሌሎች ያደርሳሉ፤ እንዳ አጵሎስ መጋቢና መምህረን የሚሆኑ ደግሞ ያመኑትን በእምነታቸው እንዲያድጉ ይረዱአቸዋል:: ሁሉም የቤተ ክርስቲያን

መሪዎች ለበለጠ ዓላማና ግብ በሕብረት መሥራት ይገባቸዋል። ይህም ግብ የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት በየጊዜው በመገምገም የእግዚአብሔር ሕዝብ በእምነቱ ሲያድግ ማየት ነው፤ (ኤፌ.4:11-13)። ሁላችንም ብንሆን የምናገለግለው መንፈሳዊ ዕድገት ሊሰጠን የሚችለውን አንዱን ኢየሱስ ክርስቶስን በመሆኑ በልባችን ከእኛ ጋር ከሚያገለግሉት ከሌሎቹ የበለጠ ክብር የመፈለግ ምኞት ሊኖረን አይገባም።

ጥያቄ 6. ሀ/ በተለያየ መልክ በመሪነት በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚያገለግሉትን ሰዎች ስም ዘርዝር ጻፍ። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያንህ ያለውን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ አብረው በሕብረት የሚሠሩት እንዴት ነው?

ለ/ አንዳንዴ ሰይጣን በመካከላቸው የምቀኝነትን ሃሳብ በማምጣት፤ የእግዚአብሔርን ሥራ የሚያደናቅፍባቸውን መንገዶች ግለፅ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎታችንን ከአገልጋዮች ወይም ከሸማገሌዎች አንፃር ሳይሆን ከእግዚአብሔር አንፃር ካላየነው አገልጋዮችን እንደ ጣዖት ተደገፍናቸዋል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «በጌታ የሚታመን አያፍርም» ይላል። ስለዚህ ከጌታ በስተቀር በሌላ የሚተማመን እንደሚያፍር ግልጽ ነው።

## 3ኛ. መንፈሳዊ ጉልምስና የአገልግሎቱን ጽካም በእግዚአብሔር ሚዛን ላይ ያስቀምጣል፤ (10-17)

ሰውን የሚያይ÷ መንፈሳዊ አገልግሎቱን በሰው መሠዊያ (ገበታ) ላይ የሚያስቀምጥ የእግዚአብሔርን ሚዛን አያይም። እርምጃው ሁሉ ሰውን ለማስደሰትና ሰው በእርሱ እንዲደሰት ነው። ይህ ሳይሳካ ሲቀር ይሰባበራል። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እኔ የእከሌ ነኝ በማለት በመከራከር ላይ ሳሉ ለራሳቸውም ለአገልጋዮቻቸውም የተዘረጋውን የእግዚአብሔርን ሚዛን ረሱ። የአገልጋዮችን ሕይወትና ጽካም መዛኙ እግዚአብሔር እንደሆነ ጳውሎስ ያስረዳል።

ሆኖም ይህን ሲል አገልጋይ በኃጢአት ሲመላለስ አይገሠጽ ማለቱ አይደለም። ኃጢአትን መገሠጽ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል፤ (1ኛ ቆሮ.5:1-2 እና 11-13)። ይህን በዚህ ክፍል ውስጥ የሚናገረው ስለ አገልግሎት ጽካም መዛኙ እግዚአብሔር መሆኑን ለማስረዳት ብቻ ነው። ስንቶች ነን «በመጨረሻ ጊዜ እግዚአብሔር ሥራዬን ገልጦ የሚመዝንበት ጊዜ ስለሚመጣ አሁን ሰውን ሳልመለከት እግዚአብሔርን በትጋት ላገለግል»

የምንል? ደግሞም ሰው ይህን ካላለ እግዚአብሔርን ማገልገል አይችልም።

በዚህ ነገር ሰው ካልተጠነቀቀ በሰው ተሰናክሎ የእግዚአብሔርን ቤት ወደ ማፍረስ ይደርሳል (16ና 17)። ያ ከሆነ ያገለገሎት ሽልማት ብቻ የማጣት ነገር ሳይሆን (14ና 15) ጠቅላላ ሕይወቱ በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ ይወድቃል። ስለዚህ ሰውን ሳይመለከቱ ማገልገል ወደ ድካም ዋጋ ከመምረቱም በላይ በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ እንዳንወድቅ ይረዳናል።

ጥያቄ 7. እኛ ስለ እግዚአብሔር ሚዛን ብናስብ ኖሮ የእኛ ወይም
የሌሎች አገልግሎት በምን ዓይነት ነበር የሚለወጠው?

እግዚአብሔርን ማገልገሉ ብቻ በቂ አይደለም፤ እንዴት እንደም ናገለግለውም ማጤኑ ተገቢ ነው። የምንሠረው ሥራ ከንጹሕ ልብ የመነጨ መሆን ይገባዋል። ሥራው የእግዚአብሔር ቤት በሆነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዘላቂ የሆነ ለውጥን ማስገኘት አለበት። በእግዚአብሔር የፍርድ እሳት ውስጥ ለእርሱ ክብር ያልሆነ ወይም ከንጹሕ ልብ ሆነን ያልሠረነው ነገር ሁሉ (እንደ እንጨት፥ ሣርና አገዳ) ምንም ጥቅም እንደሌለው ይታያል። ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ልጆች ብንሆንና ብንድንም ለሠረነው ሥራ ምንም ሽልማት አይኖርም። በትክክለኛ ንጹሕ መንፈስ ተነሣሥተን ለእግዚአብሔር ክብርና ለቤተ ክርስቲያን ጥሩ የሆነ ሥራ ከሠረን ሥራችን ዘላቂ (እንደ ብር፥ ወርቅና የከበረ ድንጋይ) ይሆናል። በተጨማሪም ከእግዚአብሔር ሽልማት እናገኛለን። በእግዚአብሔር ሚዛን ሲለካ ሥራችን የሚያሸልም እንዲሆን እስቲ ሁላችንም ሥራችንንና ልቦናችንን እንመርምር።

1ኛቆሮ.3:15:- የአማኞች ሥራ እንዴት እንደሚፈተን ነው የሚናገረው። እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታቸው እንደገና በአማኞች ላይ እንደማይፈርድባቸው ቃል ገብቷል። ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ለአማኞች ቅጣቱን ከፍሎላቸዋል (ዮሐ.5:24)። እውነተኛ አማኝ የእግዚአብሔርን ሥራ ሳይሠራ ወደ መንግሥተ ሰማይ ሊገባ ይችላል፤ ቢሆንም ይህ ሰው አሁንም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ነው። 1ኛቆሮ.6:9-10 ግን የሚናገረው የእግዚአብሔርን የዘላለም ሕይወት ስጦታ ስላልተቀበሉና ዝም ብለው በኃጢአት ኑሮ ውስጥ ያለማቋረጥ ስለሚኖሩ ሰዎች ነው።

## 4ኛ መንፈሳዊ ጉልምስና በሰው ጥበብ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጥበብ እንድናገለግል ይረዳናል፤ (18-25)

አንዳንድ ጊዜ በሰው ፊት ተወዳጅ ሆኖ ለመቅረብ ሰው ብዙ ዓለማዊ ጥበብ ይጠቀማል። ግን ይህ በእግዚአብሔር ፊት ምንም ዋጋ

የለውም። «ጌታ የጥበበኞችን አሳብ ከንቱ እንደሆነ ያውቃል»። ሰውን ማታለል ይቻላል እግዚአብሔር ግን ስለማይታለል በእግዚብሔር ቤት የዓለምን ጥበብ ማስወገድ አለብን።

ሕይወታችንን በጥንቃቄ እንጠብቅ። በእግዚአብሔር እንደምንመዘን ሳንዘነጋ በሕይወታችን እግዚአብሔርን ከማገልገል አንቦዝን። ሕይወታችን ለረስ መደሰቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ማክበሪያ ነውና በሕይወታችን እግዚአብሔርን እናክብር። «የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ የእግዚአብሔር ሕንጻ ናችሁ... የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ... ናችሁ»።

መግቢያ
----

ለወንጌል ሥራ ቅንዓት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዙውን ጊዜ ለወንጌል አገልጋዮች በቂ እንክብካቤ አያሳዩም። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ወንጌላውያንን እንድንከባከብ አጥብቆ ያስተምረናል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ተገቢውን እንክብካቤ ስላላደረገችለት የወቀሳ ጸብጸቢ ይጽፍላቸዋል። የእኛስ ቤተ ክርስቲያን ለወንጌላውያን ያላት እንክብካቤ እንዴት ነው? የዓለም ጥበብ የሚታየው ለሰዎች ወይም ለአንድ ሰው በሚሰጠው ክብር ነው። የእግዚአብሔር ጥበብ ግን ክብርን የሚሰጠው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው።

1ኛ ቆሮንቶስ 4ን አንብብ።

ጥያቄ 8. «ሎሌ» በሚለው ቃልና «መጋቢ» በሚለው ቃል መካከል ያለውን ልዩነት ግለጽ።
ጥያቄ 9. በቁጥር 4 ላይ «በዚህ አልጸድቅም እኔን የሚፈርድ ጌታ ነው» ሲል ሐዋርያው ምን ማለቱ ነው?
ጥያቄ 10. በቁጥር 6 ላይ «ስለ አንዱ በአንዱ ላይ እንዳትሁም እንዳይታበዩ (እንዳትታበዩ)» ማለቱ ምን ማለቱ ነው?
ጥያቄ 11. ከቁጥር 8 እስከ 13 ያለው ክፍል በግልጽ የሮር አጻጻፍ ነው። የጽሑፉን ጠቅላላ ሀሳብ በአጭሩ ግለጽ።
ጥያቄ 12. በቁጥር 15ና 16 ላይ «በወንጌል ወልጄአችኋለሁና እንግዲህ እኔን የምትመስሉ ሁኑ» ሲል በምን እርሱን እንዲመስሉ ነው የሚጠይቃቸው?

ከቁጥር 1-5 ያለው ክፍል ከላይ የጠቀሳቸውን ነጥቦች ይከተላል። ሐዋርያው ጳውሎስና ባልደረቦቹ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ ተጠሪነታቸው ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር መሆኑን ይገልጻል። ስለሆነም በመንፈሳዊ ሠረተኞች ዘንድ ታማኝ ሆኖ መገኘት አስፈላጊ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በረሱ ላይ እንኳ መፍረድ እንደማይችል ይናገራል። ጳውሎስ ሰው

እንደመሆኑ ሊታለል እንደሚችል ያውቅ ነበር። ስለዚህም እንኳን በሰዎች ላይ ቀርቶ በሬሱ ላይ ለመፍረድ የማይችል መሆኑን ተረድቶ ነበር። የቆሮንቶስም ክርስቲያኖች በሠራተኞች ላይ ከመፍረድ እንዲጠበቁ ያስጠነቅቃቸዋል።

ጳውሎስ ስለራሱና ስለባልደረቦቹ የእግዚአብሔር ሎሌና የእግዚአብሔር መጋቢ የሚሉትን ቃላት ይናገራል። በመጽሐፉ ሎሌ የሚባለው ተራ አሽከር ሲሆን መጋቢ ደግሞ በሎሌዎች ላይ የተሾመ የሎሌዎች ተቆጣጣሪ አሽከር ነው። ስለዚህ ሎሌም ሆነ መጋቢ ሁለቱም የእግዚአብሔር ባሮች እንጂ ባለቤቶች ስላልሆኑ ባንዱም መመካት የለብንም። ለቀጠረቻው ለእግዚአብሔር መልስ የሚሰጡ ተጠሪነታቸውም ለእግዚአብሔር የሆነ አገልጋዮች ናቸው።

በቁጥር 6 ላይ የአማርኛ ስህተት አለ፤ «እንዳይታበዩ» የሚለው «እንዳትታበዩ» ብሎ መነበብ አለበት። በቁጥር 6 እና 7 ላይ ሐዋርያው ክርስቲያኖች በሠራተኞች ላይ መመካት እንደሌለባቸው ይናገራል። የጠቀሰው ምሳሌ «ከተጻፈው አትለፍ» የሚለው ጥቅስ በብሉይ ኪዳን የትም ቦታ ተጽፎ አይገኝም፤ ምናልባት በዘመኑ በኅብረተሰቡ የታወቀ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። አገልጋዮች እግዚአብሔር በሰጣቸው ስጦታ ስለሚያገለግሉ ተገልጋዮች በአገልጋዮች ችሎታ መመካት የለባቸውም።

ጥያቄ 13. አንዳንድ ሰዎች ወይም አገልጋዮች በችሎታቸው የሚመኩ አሉ? መመካታቸውን የሚገልጹት እንዴት ነው?

ከቁጥር 8-13 ያለው ክፍል በአሽሙር መልክ የቀረበ የጳውሎስ ወቀሳ ነው። ሀሳቡን በዝርዝር ለማግኘት እንድንችል ቁጥር በቁጥር እንመለከተዋለን።

ቁጥር 8:- የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በዓለማዊ አስተሳሰብ ውስጥ ስላሉ በወንጌል ምክንያት እየተሰደዱ የሚናቁትን የወንጌልን አገልጋዮች ይንቁ ስለነበር ጳውሎስ «ነግሣችኋል» በማለት ያሽሚጥጣቸዋል። በእርግጥ የነገሡ ከሆነ ከወንጌል አገልጋዮች ጋር አብረው በነገሡ፤ ማለት አሁን ለክርስቶስ ወንጌል ታማኝ ሆነው ከአገልጋዮች ጋር በመሰለፍ በዓለማውያን ቢናቁና በኋላ በወቅቱ ከወንጌል አገልጋዮች ጋር አብረው ቢነግሡ ይሻላል ይላቸዋል።

ቁጥር 9:- ሐዋርያት የወንጌል ሥራ ቀዳምተኞች ስለሆኑ ዓለም በስደትና በማንቋሸሽም ቀዳምት አድርጋቸዋለች። በዘመኑ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ወደ ሞታቸው ሲነዱ በሰልፍ ታጅበው ሚቾቹ ከሰልፉ መጨረሻ ተደርገው በሕዝብ ይንገጠጡ ነበር። ሐዋርያው ያን ምሳሌ ወስዶ ሐዋርያት በዓለም ብቻ ሳይሆን በመላእክትም እንኳ እየታዩ በውርደት ቦታ እግዚአብሔር እንዳስቀመጣቸው ይናገራል (መላእክት የሰዎችን ሕይወት ታዛቢ ለመሆናቸው የሚያስረዱ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት፤

1ኛ ቆሮ.11:10፤ 1ኛ ጢሞ.3:16፤ 5:21፤ 1ኛ ጴጥ.1:12)። እንግዲህ የአሸሙሩ አቀጣጫ ይገባን። መንፈሳዊ አባቶች የሆኑት ሐዋርያት እንዲህ ተዋርደው ሳሉ ምእመናኑ ግን በትዕቢት ተነፍተው አገልጋዮችን ቢያንገዋልሉ ምን ያህል መጥፎ ነገር እንደሆነ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ያስረዳቸዋል።

ከቁጥር 10-13:- የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በኩራት አገልጋዮችን ሲያንገዋልሉ አገልጋዮች ግን ለክርስቲያኖች ሲሉ በብዙ ውርደትና መከራ ውስጥ አሉ። ይህ ክፍል ቤተ ክርስቲያንን ለወንጌል አገልጋዮች ተገቢ እንክብካቤ እንድታደርግ በጥብቅ ተግሣጽ ይናገረታል። ቤተ ክርስቲያንም ይህን ተግሣጽ መስማትና ወንጌላውያንን እንደቃሉ መሠረት ልትንከባከብ ይገባታል።

ቁጥር 14:- ሐዋርያው ነገሩን ለማለሳለስ በፍቅር ብቻ ተገጾ ይህን ወቀሳ እንደቀረበላቸው ያሳስባቸዋል።

ቁጥር 15:- ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን የሰበከላቸው ጳውሎስ ስለሆነ በክርስቶስ አባታቸው መሆኑን ያስታውሳቸዋል፤ ስለሆነም በግልጽ ሊወቅሳቸው ይችላል። እንዲያውም ከሱ በኋላ መጥተው ካገለገሏቸው ሞግዚቶች ይልቅ ይቀርባቸዋል። ይህ አነጋገሩ በተለይ እርሱን አንፈልግም ያሉትን ክርስቲያኖች በጣም ሊገስጻቸው ይገባል።

ቁጥር 16:- ልጅ አባቱን መምሰል እንደሚገባው የእርሱን ምሳሌ እንጂ የዓለምን ምሳሌ መምሰል የለባቸውም፤ 1ኛ ቆሮ.11:1፤ 1ኛ ተሰ.1:6፤ ሮሜ 12:1 እና 2። የጳውሎስን የክርስትና አኗኗር በሚገባ ተረድተው እርሱን እንዲመስሉ ስለ እርሱ ሕይወት የሚያውቀውን ጢሞቴዎስን ይልክላቸዋል። ጳውሎስ በስብከት ብቻ ሳይሆን በኑሮውም ያስተምር ስለነበር እኛም የዘመኑ ወንጌላውያን አርአያ የሆነ ሕይወት ሊኖረን ይገባል።

ከቁጥር 18-21:- ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚዎች በተነሡበት ጊዜ አፍሮ ወይም በመቀየም አኩርፎ ከቤተ ክርስቲያኑ የማይቀር መሆኑን በግልጽ ያውጃል። የጌታ አገልጋይ ነገሮች በጠረ መንገድ እንዲታዩ መጣር አለበት።

ጥያቄ 14. በአሁኑ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ለአገልጋዮችዋ ተክክለኛ እንክብካቤ ምን እያደረገች ነው?

## ትምህርት 2

## የ3ኛ ቀን ጥናት

### ክፍል 3. ክርስቲያን በዓለም ውስጥ እንጂ ከዓለም አይደለምI

(ምዕራፍ 5)::

#### መግቢያ

ምንም እንኳ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ጸጋ ከዓለም ርኩሰት የጸነ ቢሆንም በዓለም እስካለ ድረስ አልፎ አልፎ ዓለማዊ ፀባይ ማሳየቱ አይቀርም:: የቆሮንቶስም ክርስቲያኖች የዓለማዊ ፀባይ የሆነ የዝሙት ሥራ በመካከላቸው ተነሥቶ ነበር:: ነገር ግን ክርስቲያን በኃጢአት ሥር ስለማይኖር በንስሐ ከውድቀቱ ተመልሶ ይነሣል:: ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ግን ደግሞ ሰባት ጊዜ ይነሣል! በዚህ ተስፋ እንጽናና::

1ኛ ቆሮንቶስ 5ን አንብብ::

ጥያቄ 15. ከቁጥር 1 እስከ 2 ባለው ክፍል ውስጥ «ታብያችኋል ይልቅስ እንድታዝኑ አይገባችሁምን?» ሲል ከጠቀሰው የዝሙት ሥራ ጋር ትዕቢታቸው ምን ግንኙነት አለው?

ጥያቄ 16. ከቁጥር 3 እስከ 5 ያለውን ክፍል ከማቴ.18:15-20 ጋር በማወዳደር መግለጫ ጻፍ::

ጥያቄ 17. ከቁጥር 6-8 ላይ ስለ እርሾ የተናገረውን አብራራ::

ጥያቄ 18. ከቁጥር 9-13ን በጥንቃቄ በማጥናት የሚከተለውን ጥያቄ መልስ:: ክርስቲያን ከዓለማውያን ራሱን መለየት የለበትምI ግን ክርስቲያን ነኝ ከሚል ሕይወቱ መጥፎ ከሆነ ከሱ መለየት አለበት:: ለምን? መልስህ ገለፃ ያለው ይሁን::

የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በመካከላቸው ታላቅ ኃጢአት ሲካሄድ እንደማዘንና እርምጃ እንደመውሰድ በዓለማዊ ጥበብ እየተመኩ ተቀምጠዋል:: በመካከላቸው የነበረውም በጸሎ እንኳን በምእመናን መካከል ቀርቶ በማያምኑት መካከል እንኳ ተቀባይነት የለውም:: ከአባሎች አንዱ ከእንጀራ እናቱ ጋር በሥጋ ፍትወት ይኖር ነበር:: ስለዚህ በጸሎ ብዙም ዝርዝር አይሰጥም:: ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ዝም ማለቷ በጣም ደካማ መሆኗን ያስረዳል::

«ይህን የሠራ ከመካከላችሁ ይወገድ»:: ሐዋርያው ቤተ ክርስቲያኒቱ

ማድረግ የሚገባትን በግልጽና በአጭሩ ይናገራል። እንዴት ከመካከላቸው እንደሚያስወግዱት መመሪያ ይሰጣል።

ምእመናን በአንድነት በክርስቶስ ስምና ሥልጣን ተሰብስበው ይህን በደለኛ ከመካከላቸው ማስወገድ አለባቸው። በዚህ ስብሰባቸው ላይ ጌታ ኢየሱስ በሥልጣኑና በኃይሉ ከመካከላቸው ይገኛል። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያኑ ውሣኔ የሰዎች ውሣኔ ሳይሆን የክርስቶስ ውሣኔ ነው፤ (ማቴ.18:15-20)።

በማቴ.18:15-20 ላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ አንድ ሰው ያልተናዘዘው ኃጢአት ካለው ምን ዓይነት እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚገባን ያሳየናል። በመጀመሪያ:- ክርስቲያን የሆነ አንድ ሰው ኃጢአተኛውን ሰውዬ መውቀስ ይገባዋል። ሁለተኛ:- ሰውዬው መናዘዝ ካልፈለገ ግን በሁለት ወይም በሦስት የክርስቲያን ምስክሮች ፊት ይወስደዋል። ሦስተኛ:- አሁንም ሰውዬው አልናዘዝም ብሎ ከወሰነ፥ ለቤተ ክርስቲያን ይነገረትና ኃጢአተኛው ሰውዬ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ሕብረት እንዲቋረጥ ይደረጋል። ጳውሎስም የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሚያሳስበው ይህንን የመጨረሻ እርምጃ እንዲወስዱ ነበር።

ጥያቄ 19. እንደዚህ ዓይነት እርምጃ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ተወስዶ ያውቃል? እንዴት ተፈጸመ? በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሦስቱም ደረጃዎች ተፈጸሙ?

በቁጥር 5 ላይ ሐዋርያው ትርጉሙን ለመረዳት የሚያስቸግር ቃል ይናገራል፤ «ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዶ ነው»። ምን ማለቱ ነው? ከቤተ ክርስቲያን ጉያ መውጣት ከክርስቶስ ቤት ተባሮ ሰይጣን በነገሠበት በዚህ ዓለም ውስጥ መጣል ነው፤ ቆላስያስ 1:13፤ 1ኛ ዮሐ.5:19 ተመልከት። «ለሥጋው ጥፋት» የሚለውም በቤተ ክርስቲያን መወገዝና ክርስቶስን ማስቀየም የሥጋ መቅሰፍት ሊያስከትል መቻሉን ማስታወሱ ነው፤ (1ኛ ቆሮ.11:30፤ የሐዋ.13:8-11)። እንግዲህ የጳውሎስ ዓላማ አጥፊው በጌታ እጅ ከተገሠጸ አዝኖ ንስሐ ይገባና ነፍሱ ትድናለች ማለቱ ነው እንጂ ያለንስሐ መግባት ወደ ዓለም በመጣሉና በዓለም መከራ በመቀበሉ ብቻ ነፍሱ ትድናለች ማለቱ አይደለም።

ቁጥር 6 ላይ እንደገና ስለ ትዕቢታቸው ይናገራል። በውጭ በትዕቢት ሲረመዱ በውስጣቸው ግን ኃጢአት እንደ እርሾ እየበላቸው ነው። እርሾ በመጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአት ምሳሌ ነው፤ (ማቴ.13:33፤ ገላ.5:9)።

ከቁጥር 7-8 ከብሉይ ኪዳን የእርሾን ምሳሌ ያቀርባል። በአይሁዶች የፋሲካ በዓል ቂጣ እንጂ እርሾ ያለበት ነገር አይበላም። ይህም የግብፅን ባርነት ትተው በነፃነት እንዳሉ አዲስ ሕይወታቸውን የሚያስረዳ ነው።

አሁንም ክርስቲያኖች የዓለምን መጥሮ ሥረዎች ማስወገድ አለባቸው። «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና ስለዚህ በቅንነትና በእውነት ቂጣ በዓልን እናድርግ እንጂ በአሮጌ እርሾ በክፋትና በግፍ እርሾም አይደለም»። ክርስቲያን በክርስቶስ ሞት ከኃጢአት ባርነት ነፃ የወጣ ስለሆነ እንደገና ወደ ባርነት ለኃጢአት ሥረ ሬሱን መሸጥ የለበትም፤ (ሮሜ 6:12-14)።

ከቁጥር 9-13 ባለው ክፍል ውስጥ ከዚህ በፊት የጻፈላቸውን መልእክት በደንብ እንዳልተረዱና አሁን እንደገና ሊያስረዳቸው እንደሚሞክር እንገነዘባለን። የትምህርቱ ዋና ፍሬ ነገር በቁጥር 12ና 13 ላይ ይገኛል። «በውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ አትፈርዱምን? በውጭ ባሉቱ ግን እግዚአብሔር ይፈርዳል። ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት»። ክርስቲያን በዓለም እንጂ ከዓለም አይደለም፤ (ዮሐ.17:15 እና 16)። ስለዚህ በጣዖት አምልኮአቸው እስካልተጠላለፈ ድረስ ክርስቲያን ከዓለም ሰዎች ጋር አብሮ መኖር አለበት። ነገር ግን ክርስቲያን ነኝ እያለ በእግዚአብሔር መንገድ የማይመላለስ ከሆነ እንደዚህ ካለው ጋር እንኳን ለአባልነት በቤተ ክርስቲያን መቀበል ቀርቶ በኅርብትና እንኳ መወዳጀት ክልክል ነው። እንድ አማኝ ከቤተ ክርስቲያን በቅጣት ከአባልነት ከተወገደ በኋላ ከእርሱ ጋር አባሎች በውጭ መወዳጀት የለባቸውም። እንዲህ ካደረጉ የቤተ ክርስቲያኒቱን ተግሣጽ በማክሸፍ ይበርዙታል። በቤተ ክርስቲያን የእርሱን መወገድ ደግፈው ዞር ብለው ግን በውጭ ጓደኝነታቸውን ቢቀጥሉ ወላዋይና መንታ ምላስ ያላቸው ቀላማጆች መሆናቸው ነው። የተገሰጸውም ሰው የተግሣጹን ትልቅነት ባለመረዳት ንስሐ እንዳይገባ እንቅፋት ይሆኑበታል። ስለዚህ ይህን የሐዋርያውን ቃል በጥንቃቄ እንገንዘብ።

ጥያቄ 20. ክርስቲያን ነኝ እያለ ግን በኃጢአት ውስጥ ለሚኖረው ሰው ሕብረታችንን ማቋረጣችንን የምንገልጸው እንዴት ነው? በምሳሌ ግለጽ።

## ትምህርት 2

### የ4ኛ ቀን ጥናት

**ክፍል 4. የምእመናን የእርስ በርስ መካሰስ (6:1-11)**

<u>የንባብ ክፍል</u>:-1ኛቆሮ.6:1-11ን

ጥያቄ 21. በቁጥር 1 ላይ «በቅዱሳን ፊት መፋረድ» ሲል ቅዱሳን የሚላቸው እነማንን ነው? አመፀኞችስ ያላቸው እነማን ናቸው?

ጥያቄ 22. ከቁጥር 1-8 የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የፈጸሟቸው ስንት ስሕተቶች ተዘርዝረዋል? ምን ምን ናቸው?

ጥያቄ 23. ከቁጥር 9-11 ያለው ከቁጥር 1-8 ካለው ጋር የሃሳብ ዝምድናውን አስረዳ።

ቁጥር 1፡- በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አማኝ ከአማኝ ጋር ይካሰስ ነበር። በተካሰሱም ጊዜ ለዳኝነት አማኞች ዘንድ ሳይሆን እማያምኑት ዘንድ ይሄዱ ነበር። ይህ እንኳን በክርስቲያን መካከል ቀርቶ በአይሁድ ባሕል እንኳ ተቀባይነት አልነበረውም። ጳውሎስም ይህ በክርስቲያኖች መካከል መደረግ እንደሌለበት ያስተምረል። በዚህ ክፍል ውስጥ አማኞችን ቅዱሳን ሲላቸው የማያምኑትን ደግሞ አመጸኞች ይላቸዋል። አመጸኝነታቸው ለእግዚአብሔር ሕግና በወንጌል በኩል ለቀረበው ለእግዚአብሔር ምሕረት ባለመታዘዛቸው ነው።

ከቁጥር 2-3፡- አማኞች በፍርድ ቀን ከክርስቶስ ጋር በመተባበር በዓለም ላይ ይፈርዳሉ፣ (ዳንኤል 7:22፣ ማቴ.19:28)። እንግዲያስ በአሁኑ ጊዜ በሚነሡ ክሶች ላይ መፍረድ ይችላሉ። ስለ ትዳር ጉዳይ ቀርቶ «በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ» እግዚአብሔር ወስኗል። በመላእክት ላይ መፍረድ ማለትም በመላእክት ላይ መሠልጠን ማለት ነው። ወይም በመላእክት ላይ ሥልጣን መያዝ ማለት ነው። ይህም ሊሆን የሚችለው አማኝ ከክርስቶስ ጋር ስለሚነግሥ ክርስቶስም በመላእክት ላይ ስለነገሠ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ እንደመሆኗ መጠን ይህን ሥልጣን ከክርስቶስ ጋር ትካፈላለች፣ (ሮሚ 8:17፣ ኤፌ.1:22)።

ከቁጥር 4-5፡- ቁጥር 4ን አንዳንድ የግሪክ ቋንቋ ሊቃውንት እንዲህ ብለው ይተረጉማሉ፣ «እንግዲህ ስለትዳር ጉዳይ የፍርድ ቤት ቢያስፈልጋቸሁ በቤተ ክርስቲያን የተናቁትን ሰዎች ፈረጆች አድርጋቸሁ አስቀምጡ።» እንዲህ ከተወሰደ ትርጉሙ «ምንም እንኳ ለዳኝነት የሚበቁ አማኞች በመካከላችሁ ባይገኙም ዓለማውያን ፊት ሄዶ ከመፋረድ በቤተ ክርስቲያን ዝቅተኛው አማኝ የተሻለ ፍርድ ይሰጣልና እርሱን ሹሙት» ማለት ይሆናል። ነገር ግን ይህ አተረጓጎም ትክክለኛ አይደለም። ትክክለኛው ትርጉም የአማርኛው ትርጉም ስለሆነ በዚያው እንረጋለን። ጳውሎስ ጥያቄ ነው ያቀረበው፣ «በቤተ ክርስቲያን የተናቁትን ሰዎች ፈረጆች አድርጋቸሁ ታስቀምጣላቸሁን?»። ማለት ዓለማውያን በቤተ ክርስቲያን የተናቁና የአማኝን ሕይወት በጸንብ የማያውቁ ሰዎች ስለሆኑ በአማኝ ላይ በፍርድ እንዲቀመጡ አማኝ እነርሱ ዘንድ መሄድ የለበትም። በቁጥር 5ም ላይ በትዳር ጉዳይ የሚፈርዱ አማኞች የማይጠፉ መሆኑን አጠረጣሪ እንዳልሆነ ያረጋግጣል።

ጥያቄ 24. በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ በሁለት ክርስቲያኖች መካከል ክርክር ቢነሣ የሚታረቁት በምን መንገድ ነው?

ከቁጥር 6-8:- በዚህ ክፍል ሐዋርያው በመሠረቱ የመካሰስ ነገር በመካከላቸው መኖሩት እንደሌለበት ይናገራል። ይህ በመሆኑ በክስ እንኳ ቢረቱ እንደተሸነፉ ያስረዳቸዋል። አማኝ ከክርስቲያን ወንድሙ ጋር በሰላም መኖር አለበት። ቢካሰስ ጽካም መሆኑን መገንዘብ አለበት። ግን በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክስ የተነሣው ወንድም ወንድሙን ስለሚያታልል ነበር። ይህ መሆን አልነበረበትም። ስለዚህ በዚህ በመካሰስ ጉዳይ የፈጸሚቸው ስሕተቶች እነዚህ ናቸው:-

1ኛ/ አማኞች እርስ በርስ መፋቀርና መደጋገፍ ሲገባቸው በውስጣቸው ክስ መኖሩ።

2ኛ/ ክሱም ስለተበደሉ ሳይሆን ወንድሞችን በማታለል ነበር።

3ኛ/ ይህንም ክስ በአማኞች ፊት ሳይሆን በማያምኑ ፊት ያቀርቡ ነበር።

ከቁጥር 9-11:- አማኞች ክሳቸውን በማያምኑ ፊት ያቀረቡት በአማኝና በማያምን መካከል ምን ያህል ትልቅ ልዩነት እንዳለ ባለመረዳት ሊሆን ስለሚችል፥ ያለውን ልዩነት በዝርዝር ያስረዳቸዋል። «አመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም»። አመፀኝነታቸው በሁለት መንገድ ነው። 1ኛ/ የእግዚአብሔርን ሕግ በሕይወታቸው አይጠብቁም። 2ኛ/ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ያቀረበላቸውን ጸጎነት አይቀበሉም። ስለዚህ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ሕጉንም እንዴት እንዳፈረሱ በዝርዝር ጽፎአል (ቁጥር 9 እና 10)። በቁጥር 11 ላይ የክርስቲያንን መለወጥ ያስተምራል። «ከእናንተም አንዳንዶች እንዲዚህ ነበራችሁ»። አሁን ግን:-

1ኛ. <u>ታጥባችኋል፤</u> ክርስቲያን ከኃጢአቱ እድፍ በክርስቶስ ደምና በመንፈስ ቅዱስ ታጥቧል። ጥምቀት የዚህ የመታጠብ የውጭ ምሳሌ ሆኖ ቀርቧል። ኃጢአት እድፍ ወይም እርኩስ ነው፤ ስለዚህ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሚኖረው ከእድፉ ሲታጠብ ብቻ ነው። ይህም በሥራ ሳይሆን እንዲያው በነፃ በክርስቶስ በማመናችን ብቻ ይሰጠናል።

2ኛ. <u>ተቀድሳችኋል፤</u> መቀደስ ሁለት ደረጃ አለው። የመጀመሪያው ደረጃ አማኝ ክርስቶስን የተቀበለ ዕለት በእግዚአብሔር መንፈስ ታጥቦ የእግዚአብሔር ዕቃ ይሆናል። ቅዱስ ዕቃ ነው፤ (3:16 እና 17)። ይህ የሚደጋገም ሳይሆን በአማኝ ሕይወት አንድ ጊዜ ስለተፈጸመ አማኝ ቅዱስ ይባላል፤ (1:2፤ 6:1)። ሌላው የቅድስና ደረጃ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ አማኝ ከኃጢአት ነፃ ይሆናል። አሁን አማኝ ከኃጢአቱ ንጹሕ ላለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስም ሕይወቱም ይመሰክራሉ፤ (1ኛ ዮሐ.1:8-10)። ነገር ግን ተቀድሳችኋል ማለቱ የሁለተኛውን ዓይነት ቅድስና ሳይሆን የአንደኛውን ዓይነት ቅድስና ማለቱ ነው።

3ኛ. <u>ጸድቃችኋል፤</u> ይህ የፍርድ ቤት ቋንቋ ነው። አማኝ በእግዚአብሔር ፍርድ ዙፋን ፊት ቀርቦ ክሱ ተሰርዞለት የክርስቶስን ጽድቅ

በመነናጸፍ «ጸድቅ» ተብሎ ተፈርጾለታል። ስለዚህ ስለ ኃጢአቱ ወጸፊት በፍጹም አይጠየቅም። ይህ ወንጌል የሚሰጠን የምሥራች ነው። ይህን የምሥራች በእምነት የተቀበለ ሁሉ የዚህ ጽድቅ ወራሽ ሆኖአል። እንግዲህ አማኝ ይህን መሰል ሲሆን የማያምን ደግሞ የረከሰና በእግዚአብሔር ፍርድ ሥር ያለ ስለሆነ እንዴት አማኝ ለጻኝነት ጉዳይ ወደማያምን ዘንድ ይሄድ?

## ትምህርት 2

### የ5ኛ ቀን ጥናት

በዚህ ሳምንት ጥናት ላይ ክለሳ አድርገህ የመወያያ ጥያቄዎችንም በጥናት መልክ ሠርተህ ከጨረስክ በኋላ ራስህን ለሳምንታዊ ስብሰባ አዘጋጅ።

### ሳምንታዊ ስብሰባ

ለመሪው:- ባለፈው ሳምንት ለሳምንታዊው ስብሰባ የተሰጡትን መመሪያዎች ተከተል። በውይይቱ ጊዜ እያንዳንዱ ተማሪ መልሱን እንዲናገር አድርግ።

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ:- ከተማሪዎቹ ጋር ሊካፈለው የሚችል በዚህ ሳምንት የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚገኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወይም ሃሳብ በመምረጥ የስብሰባው መሪ ከ5-10 ደቂቃ ያህል የሚወስድ የስብከት ጊዜ ማዘጋጀት አለበት።

2. ፀሎት:- አብረቻሁ ለ10 ደቂቃ ያህል ስለ እያንዳንዳችሁና ስለ ቤተ ክርስቲያን ችግር ፀልዩ።

3. ክለሳ:- ለ15 ደቂቃ ያህል የዚህን ሳምንት ትምህርት ጠቅለል ባለ መልኩ ተመልከቱት (ክለሳ አድርጉ)።

መምህር:- እያንዳንዱ ተማሪ ሳምንታዊ ትምህርቱን ማጠናቀቁንና በደንብ መረዳቱን ይዩ። እያንዳንዱ ተማሪ ከትምህርቱ የተማረውን ነገር በዝርዝር ይጻፍ።

የስብሰባው መሪ:- በዚህ ሳምንት የትምህርት ክፍል ላይ የተመሠረተ ትንሽ ፈተና ብትሰጣቸው ይመረጣል።

4. ውይይት:- ለ25 ደቂቃ ያህል የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው። ሁሉም ሰው የራሱን ሃሳብ ማካፈሉን እርግጠኛ ሁን። የእነዚህን ጥያቄዎች ተግባራዊነት በማሳየት ተማሪዎቹ ሰፋ ያለ አመለካከት

እንዲኖሩቸው አድርግ።

1ኛ/ በክርስቶስ ሕፃን በመሆንና በሥጋዊነት መካከል ያለውን መመሳሰልም ሆነ መለያየት አስረዳ።

2ኛ/ ሀ. በመንፈሳዊ ነገር መጐልመስ የሚያስከትለውን ዘርዝር።
ለ. እኛና በእኛ ኃላፊነት ሥር ያሉት ምዕመናን እንዲጐለምሱ ምን ማድረግ አለብን?

3ኛ/ ሀ. አገልጋይ የእግዚአብሔር ሎሌና መጋቢ መሆኑን መገንዘቡ ለምን ይረዳዋል?
ለ. ስለ አገልግሎታችን ምን አዲስ ሃሳብ ይሰጠናል?
ሐ. አገልግሎታችንን እንዴት አድርጎ ነው የሚያሳድገው?

4ኛ/ ሀ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ንስሐ ሳይገቡ ኃጢአት የሚያዘወትሩ አባሎች በተግሣጽ ካልተወገዱ በቤተ ክርስቲያኑ ላይ ምንን ያስከትላሉ?
ለ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በኃጢአት የሚመላለሱትን ለመቅጣት ምን ዓይነት እርምጃዎችን ነው መከተል ያለብን?

5ኛ/ ሀ. በቆሮንቶስ አማኞች መካከል ክስ መነሣቱ ስንት ጉድለቶች ያሳያል? ምንድናቸው?
ለ. እነዚህ ጉድለቶች ምን በዘመናችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ነው የሚታዩት?

5. <u>ፀሎት</u>፡- የተማረችሁትን ነገር ተግባረዊ እንድታደርጉት በፀሎት የእግዚአብሔርን ዕርዳታ በመጠየቅ ስብሰባችሁ ዝጉ።

## ትምህርት 3

### የ1ኛ ቀን ጥናት

### <u>ክፍል 5. የአማኝ አካልና ዝሙት (6:12-20)</u>

ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ሙሴ «አትስረቅ»፥ «አትግደል»፥ «አትመኝ»፥ «አታመንዝር» በማለት ሕግን ብቻ አይደረድርም። ነገር ግን ክርስቲያን ከኃጢአት ለምን መራቅ እንዳለበት በማስረዳት ኃጢአትን ይከለክላል። ስለ ዝሙት ሰፊ ትምህርት በመስጠት ክርስቲያን ከዝሙት መራቅ ብቻ ሳይሆን ክርስቲያን <u>ለምን</u> ከዝሙት መራቅ እንዳለበት ያስረዳል።

1ኛ ቆሮንቶስ 6:12-20ን በጥንቃቄ በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ::

ጥያቄ 1. በቁጥር 12 «ሁሉ ተፈቅዶልኛል ሁሉ ግን አይጠቅምም» የሚለውን ሃሳብ አብራራ::
ጥያቄ 2. በቁጥር 12 «ሁሉ ተፈቅዶልኛል በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም» የሚለውን አብራራ::
ጥያቄ 3. በቁጥር 13 እና 14 ላይ መብል ለሆድ ከሆነ ሥጋ ለዝሙት አለመሆኑን ጳውሎስ እንዴት ያረጋግጣል?
ጥያቄ 4. ከቁጥር 15 እስከ ቁጥር 17 ሁለት ዓይነት «አንድነቶች» ተጠቅሰዋል፤ ምን ምን ናቸው?
ጥያቄ 5. በዚህ ክፍል ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ዝሙትን በተለያዩ ምክንያቶች ይከለክላል፤ እነዚህን ምክንያቶች ዘርዝር፤ (ቁጥር 15-20::)

ከቁጥር 12-14:- የቆሮንቶስን ምእመናን ጳውሎስ ስለክርስቲያን ነፃነት «ሁሉ ተፈቅዶልኛል» በማለት ሳያስተምራቸው አይቀርም:: እነርሱ ግን ይህን ትምህርት አጣመሙ:: ሁሉ ከተፈቀደ እንግዲያስ ዝሙትም መከልከል የለበትም ማለት ሳይጀምሩ አይቀሩም:: ስለዚህ ጳውሎስ «ሁሉ ተፈቅዶልኛል ሁሉ ግን አይጠቅምም» የሚለውን ሃሳብ መጨመር ነበረበት:: በተጨማሪም ሰው በክርስቶስ ነፃነቱ የጽድቅና የቅድስና አገልጋይ እንዲያደርገው ነው እንጂ የኃጢአት ባሪያ በመሆን ራሱን ለዝሙትና ለመሳሰሉት ኃጢአቶች እንዲሸጥ አይደለም፤ (ሮሜ 6:13-14)::

ምንም እንኳን በአንዳንድ ነገሮች ላይ ነፃነት እንዳለን ብናውቅም እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች መጠየቅ ይገባናል:: አንደኛ:- ይህ የማደርገው ነገር ለሥጋዬ÷ ለመንፈሳዊ ሕይወቴ÷ ለምስክርነቴ÷ ወዘተ የሚጠቅም ነው ወይ? መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃወም ማንኛውንም ነገር መተው ይገባናል:: ሁለተኛ:- ይህ ነገር እኔን እየገዛኝ ወይም እየሠለጠነብኝ ነው? ብሎ መጠየቁ ተገቢ ነው:: እኛ የክርስቶስ አገልጋዮች እንጂ የሌላ ነገር ተገዢ መሆን አይገባንም:: ኃጢአት ሊቆጣጠረን አይገባም:: ጥሩ ነው ብለን የምንለው እንደ ምግብ ያለ ነገር እንኳን ሃሳባችንንና ፍላጎታችንን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር የለበትም::

ጥያቄ 6. የትኞቹ መጥፎ ወይም መልካም ነገሮች ናቸው÷ ሰውን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ለራሱና ለወንጌል እንቅፋት የሚሆኑት?

በቆሮንቶስ ሕዝብ መካከል «መብል ለሆድ ነው ሆድም ለመብል ነው» የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር ሳይኖር አይቀርም:: የቆሮንቶስም አማኞች ይህን ምሳሌ በመመርኮዝ «ሥጋ ለዝሙት ነው ዝሙትም ለሥጋ ነው»

ሳይሉ አይቀሩም። ይህንን አስተሳሰባቸውን ሐዋርያው «ሥጋ ግን ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም» ብሎ ይቃወማል። አሁን ክርስቲያን ስለሆኑ ሥጋ ለዝሙት መሆኑ ቀርቶ ለጌታ ሆኖአል። ስለዚህ አሁን ክርስቲያን በሥጋው እግዚአብሔርን ማክበር አለበት። የክርስቲያን ሥጋ ለትንሣኤ ክብር ስለታጨ ሥጋችን በክብር ላይ መዋል አለበት። እግዚአብሔር ጌታን ከሞት እንዳሥነሣው ሁሉ የእኛንም ሥጋ ከመቃብር ያሥነሳል።

ከቁጥር 15-17:- ዝሙት እግዚአብሔር ለጋብቻ የመሠረተውን ባልተፈቀደ መንገድ በሥራ ላይ ያውላል። አንድ ወንድ ከሴት ጋር በሥጋ ፍትወት ሲገናኝ ከእርሷ ጋር አንድ አካል ይሆናል። ይህ ዓይነት ኅብረት የተፈቀደው ለጋብቻ ብቻ ነው። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ጋብቻ ሲመሠርት «ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ» ብሏልና ሚስት ካልሆነች ሴት ጋር በሥጋ መገናኘት ይህን አንድነት በተከለከለ ሁኔታ መመሥረት ነው። ስለዚህ ሐዋርያው «ከዝሙት ሽሹ» ይላል። ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር መንፈሳዊ ኅብረት መሥርቷል። ከጌታ ጋር አንድ መንፈስ ሆኖአል። እንዲህ ከሆነ በዝሙት መሠማረት በእግዚአብሔር የተከለከለ ነው።

ቁጥር 18:- የዝሙት ኃጢአት ከሌሎቹ ኃጢአቶቹ ሁሉ ኃጢአተኛውን በቀጥታ ይጎዳዋል። ምክንያቱም አካሉን ከጌታ ወስዶ «ከጋለሞታ ጋር» ስለሚያስተባብር ነው። ስለዚህ ሰው የዝሙትን ኃጢአት በጥብቅ ማስወገድ አለበት። ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸም የሥጋ ግንኙነት ሁልጊዜ ዝሙት ነውና ዝሙትን በሁሉም መንገድ ክርስቲያን ማስወገድ አለበት።

ከቁጥር 19-20:- ክርስቲያን ከዝሙት እንዲርቅ ሌላ ተጨማሪ ምክንያት ይሰጠዋል፤ የክርስቲያን አካል የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው። እያንዳንዱ እውነተኛ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስን የተቀበለ ስለሆነ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሆኖአል። ስለዚህ ትምህርት በተጨማሪ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ፤ (1ኛ ቆሮ.3:16ና 17፤ ሮሜ 8:9 እና 15፤ ኤፌ.4:30፤ ቲቶ 3:4-7)።

ከአሥርቱ ትእዛዛት አንዱ «አታመንዝር» የሚለው ነው። አሁን በአዲስ ኪዳን ትእዛዙ መሻር ቀርቶ የትእዛዙ ጥብቅነት በአምስት ምክንያቶች ላይ ተመሥርቷል። እነዚህ አምስት ምክንያቶች እንደሚከተሉት ናቸው፤

1ኛ. የክርስቲያን አካል ከጌታ ጋር ስለተባበረ ሥጋውን በዝሙት ሥራ ማርከስ የለበትም፤ (ቁጥር 13 እና 15)።

2ኛ. የክርስቲያን ሥጋ ለክብር (ለትንሣኤ) ስለታጨ በረከሰ ሥራ ላይ መዋል የለበትም፤ (ቁጥር 14)።

3ኛ. በዝሙት መሠማረት አካልን ከአመንዝራ ጋር ስለሚያስተባብር የዝሙት ሥራ መወገድ አለበት።

4ኛ. ከሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ የዝሙት ሥራ ስለሚጎዳ ሰው ከዝሙት መሸሽ አለበት።

5ኛ. ሥጋችን የመንፈስ ቅዱስ ቤት ስለሆነ በሥጋችን እግዚአብሔርን ማክበር አለብን፤ ዝሙት እግዚአብሔርን ያስቀይመዋል እንጂ አያከብረውም፤ (19-20)። ዕብ.13:4 ጋብቻ ክብር፥ አመንዝረነት ግን በእግዚአብሔር የተከለከለ መሆኑን ያስተምረል። ስለዚህ ጋብቻ ከመመሥረቱ በፊትም ሆነ በኋላ ከጋብቻ ውጭ የሥጋ ፍትወት መወገድ አለበት።

ጥያቄ 7. ሀ/ በቤተ ክርስቲያን የዝሙት ሥራ እንዲህ በጣም የበዛው ለምንድነው?
ለ/ ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነትን እንዳይለማመዱ ወጣቶቻችንን እንዴት አድርገን ነው በተሻለ መንገድ ልናስተምር የምንችለው?

## ትምህርት 3

### የ2ኛ ቀን ጥናት

### ክፍል 6. ስለ ጋብቻ ምክር (ምዕረፍ 7)

ቁጥር 1-16 ላገቡት ምክር

የንባብ ክፍል፦ 1ኛቆሮ.7:1-16ን

ጥያቄ 8. በምን ዓይነት ነው መንገድ ይህ ትምህርት ዛሬ ላሉት ወጣቶች፥ ለተጋቡት፥ ወዘተ ጠቃሚ ሊሆን የሚችለው?

ጥያቄ 9. በቁጥር 1 ላይ «ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው» ሲል ሐዋርያው ምን ማለቱ ነው?

ጥያቄ 10. ዝሙትን ለማስወገድ ጋብቻ ተሰጥቷል በማለት ሐዋርያው ሲያስተምር የጋብቻ ዓላማ ለዚህ ብቻ ነው ማለት ነው? ለመልስህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ስጥ።

ጥያቄ 11. በቁጥር 4 ላይ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም» ሲል ምን ማለቱ ነው?

ጥያቄ 12. በቁጥር 6 ላይ «እንዲፈቀድ እንጂ እንደ ትእዛዝ አልልም» ሲል ምን ማለቱ ነው?

ጥያቄ 13. ከቁጥር 10-15 ባለው ክፍል ውስጥ «አትለያይ»፥ «አይተዋት»፥ «አትተወው»፥ «ቢለይ» እያለ ሲናገር

ጋብቻንና መፋታትን በመመልከት ለእነዚህ ቃላት ትርጉም ስጥ።

ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሐዋርያውን ብዙ ጥያቄዎች ጠይቀውታል። ለመጀመሪያው ጥያቄአቸው በዚህ ክፍል መልስ መስጠት ይጀምራል።

ቁጥር 1 እና 2:- በባሕላቸው አለማግባት እንደ ትልቅ ጽድቅ ይቆጠር ስለነበር አለማግባት ወይም «ከሴት ጋር አለመገናኘት» መልካም ነው፤ ብሎ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በመጠኑ በሃሳቡ ይስማማል። ግን ሰው ይህን መልካም ነገር አገኛለሁ ብሎ ራሱን ባለመግዛት በዝሙት እንዳይጠመድ ያስጠነቅቃል።

ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን መውጫ ንቆ ቢጠመድ በእግዚአብሔር ፍርድ ሥር ይወድቃል። ያለሚስት ለመኖር ሰው ራስን የመቆጣጠር ችሎታ ከእግዚአብሔር የተሰጠው መሆኑን ማጣራት አለበት፤ (ቁጥር 7 እና ማቴ.19:11-12 ተመልከት)።

«ለራሱ ሚስት ትኑረው፤ ለራስዋ ባል ይኑራት» ሲል አንድ ወንድ ለአንድ ሴት እንጂ «ለራሱ ሚስቶች ይኑሩት» ባለማለት ከአንድ በላይ ማግባትን ይከለክላል።

ቁጥር 3-4:- «ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፤ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም»። ይህ አነጋገር በባልና ሚስት መካከል እኩልነት ያለ መሆኑን ያስገነዝበናል። ባል ሚስቱን የራሱ ስሜት ማርኪያ ዕቃ አድርጎ መጠቀም የለበትም። ነገር ግን ራሱን ለሚስቱ እርካታ እንደ አገልግሎት አድርጎ ማቅረብ እንዳለበት ይህ ሐዋርያዊ ቃል ያስተምረናል። ሚስትም ለባልዋ እንዲሁ በማድረግ በጋብቻቸው መተሳሰብን ማሳየት አለባቸው።

ጥያቄ 14. ይህ ነገር እንዴት ነው ዛሬ ስለ ባልና ሚስት ካለው ሃሳብና ባሕል ጋር ሊቃረን የሚችለው?

ቁጥር 5:- «እግዚአብሔርን አገለግላለሁ» ብሎ ሰው ሚስቱን ቢተው አገልግሎቱ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት አይኖረውም። በቃሉ የነገረንን ትእዛዝ በመናቅ እግዚአብሔርን ማገልገል አንችልም። በዚህ ላይ ሐዋርያው ባልና ሚስት መለያየት እንዳሌለባቸው ያዛል። መለየት የተፈቀደውም ለጾምና ለጸሎት ብቻ ያውም በስምምነትና ለአጭር ጊዜ ብቻ መሆኑን ማስተዋል አለብን። ባልየው ወይም ሚስትየዋ ያሰቡት ሃሳብ ሌላውን ቅር ካሰኘ ሃሳቡ መሰረዝ አለበት።

«ሰይጣን እንዳይፈታተናቸሁ» በማለት ሐዋርያው ስለመለያየት ወይም ስለመከላከል ይናገራል። ባል ወይም ሚስት በሆነው ምክንያት እርስ በርስ ቢከለከሉ፥ የተከለከለው ወገን በሰይጣን ፈተና ቢወድቅ የወደቀውም፥ በመከልከል ፈተናውን ያስከተለውም በእግዚአብሔር ፊት ጥፋተኛ ናቸው። ስለዚህ ከላይ በቁጥር 3 እና 4 ላይ የተሰጠውን መምሪያ ባልና ሚስት በጥንቃቄ መከተል አለባቸው።

ቁጥር 6:- ሐዋርያው ለጾምና ለጸሎት እርስ በርስ መለያየት እንደሚቻሉ በቁጥር 5 ላይ ተናገርአል። ይህን ንግግሩን በፈቃዳቸው እንጂ ነገሩን እንደ ትእዛዝ ቆጥረው «መጾምና መጸለይ ስላለብን መለያየት አለብን» ብለው የግዴታ እርምጃ መውሰድ እንዳይጀምሩ ቁጥር 6ን ጨምሮ ይጽፋል።

ቁጥር 7ን ከላይ ቁጥር 2ን ስንዘረዝር ጠቅሰነዋል። ሳያገቡ በንጽሕና መኖር ለሁሉ ያልተሰጠ መሆኑን ያስጠነቅቃል። እርሱ ራሱም ይህ ሳያገቡ በንጽሕና የመኖር ስጦታ እንደተሰጠው ይመሰክራል።

ከቁጥር 8-9:- በዚህ ክፍል ውስጥ ሐዋርያው ላላገቡና ለመበለቶች ምክር ይሰጣል። ሳያገቡ መኖር ተመራጭ ለመሆኑ ጌታችንም በወንጌል ተናገርአል፤ ነገር ግን ይህ ለተሰጣቸው እንጂ ለሁሉ ስላልሆነ ሰው ባለማግባት ራሱን በፈተና ላይ መጣል የለበትም። ማግባት አለበት። ይህ ትምህርት በወንጌል ጌታችን እንዳስተማረው ስለተጠቀሰ ሐዋርያው «እኔ ግን አላዝም ጌታ እንጂ» ይላል። ይህን ሲል በሐዋርያነቱ ለክርስቲያኖች ትእዛዝ ለመስጠት መብት የለውም ማለት አይደለም።

ቁጥር 10 እና 11:- ባልና ሚስት መለያየት የለባቸውም። መለያየት ቢመርጡ ግን ሳያገቡ በነጠላ ኑሮ መኖር አለባቸው። «ሚስትም ከባልዋ አትለያይ፤ ባልም ሚስቱን አይተዋት።» ይህ ትእዛዝ ሁለቱም ክርስቲያኖች ለሆኑ ነው የተሰጠው። ሐዋርያው ይህ ትእዛዝ በጌታችን የተሰጠ መሆኑን ይናገራል። የጌታም ትምህርት በወንጌል ውስጥ ተጽፎ ይገኛል፤ (ማቴ.5:32፤ 19:3-9)። እንግዲህ በዚህ ላይ የምንመለከተው ጋብቻን መተው አንድ ራሱን የቻለ በደል ነው፤ «ሚስትም ከባልዋ አትለያይ፤ ባልም ሚስቱን አይተዋት።» ግን ከዚህ የበለጠው ሁለተኛው ደረጃ በደል አለ፤ ያም እንዲህ እንቢ ብሎ ከተለያዩ በኋላ ሌላ ማግባት ነው። ይህንንም ሐዋርያው «ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር ወይም ከባልዋ ትታረቅ» ብሎ ይከለክላል።

ስለመፋታት ሊነገር ያለውን ሁሉ ሐዋርያው እዚህ አይዘረዝረውም። ለምሳሌ ጌታችን «ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ» ያለውን ሐዋርያው አይጠቅስም። ያልጠቀሰበትም ምክንያት እዚህ የሚናገረው የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የጠየቁትን ለመመለስ ብቻ እንጂ ስለ ጋብቻ ዝርዝር

ትምህርት ለመስጠት ስላልሆነ ነው። እኛ ግን ያንንም ጨምረን ማየት አለብን።

ከቁጥር 12-16:- የተቀላቀለ ጋብቻ ማለት ባል ወይም ሚስት ሳያምኑ ሲቀሩ ነው። በመጀመሪያውም ሁለቱም አማኞች ሳይሆኑ በኋላ ግን አንደኛው በወንጌል ካመኑ ማለቱ ነው እንጂ ክርስቲያን ያላመነቸውን በማግባት የተቀላቀለ ጋብቻ ማለቱ አይደለም።

እንዲህ ባለ ጋብቻ ውስጥ የማያምነው ወይም የማታምነው ለመለየት ብትፈልግ አማኝ መጨነቅ የለበትም። «ወንድም ቢሆን ወይም እህት እንዲህ በሚመስል ነገር አይገዛም።» አይገዛም ማለቱ አይታሰሩም፥ ነፃ ናቸው ማለቱ ነው። ይህ ከሆነ አማኙ ሌላ ለማግባት እንደተፈቀደለት እንገነዘባለን። ያም በጌታ የሆነ ጋብቻን ለመመስረት እድል ስለሚሰጥ የማያምን ባለማግባት ደግመኛ በተመሳሳይ ወጥመድ መውደቅ የለበትም። ይሁን እንጂ አማኝ ለጋብቻው መፍረስ ምክንያት መሆን የለበትም። «ያላመነች ሚስት ከእርሱ ጋር ልትቀመጥ ብትስማማ አይተዋት።» አማኝ «አሁን እኔ አማኝ ነኝ አንቺ ግን አታምኚም፤ ስለዚህ ከአንቺ ጋር በጋብቻ ታስሬ መኖር አልፈልግም» ሊል አይገባውም። እንዲህ ታግሦ መኖር ምናልባት የማያምነውን ወገን ወደ እምነት ሊያመጣ ይችል ይሆናል፤ «አንቺ ሴት ባልሽን ታድኚ እንደሆንሽ ምን ታውቂያለሽ?»።

ምናልባት ከማያምን ጋር በጋብቻ ታስሮ መኖር አማኙን የሚያረክስ መስሎ ታይቷቸው ሳይሆን አይቀርም፤ ምክንያቱም ሐዋርያው «ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሷልና» ይላል። ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ፥ አማኝ ከማያምን መለየት አሁንም በአንዳንዶች ዘንድ እንደሚገኝ ይሰማል። ማንም በመንፈስ ቅዱስ ተመሪሁ ብሎ ይህንን የሐዋርያውን ቃል በመናቅ ከማታምን ሚስቱ መለየት የለበትም። ይህ ከፈሪሳውያን የበለጠ ግብዝነትና የዲያብሎስ ትምህርት እንጂ የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት አይደለም። አማኝ ከማያምን ባሏ ጋር በጋብቻ ብትኖር የእርሷ ቅድስና እሱን ይባርከዋል እንጂ የእርሱ አለማመን እሷን አያረክሳትም።

ይህ የመቀደስ አነጋገር ከአማኝ ልጆች ቅድስና አንጻር የተነገረ ነው። «ልጆቻችሁ የተቀደሱ ናቸው»። የአማኝ ልጆች በወላጆቻቸው እምነት ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ወረሾች ለመሆናቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፤ (ዘፍ.17:7)። ስለሆኑም እንደ ክርስቲያን በጌታ ትምህርትና ተግሣጽ ሊኮተኮቱ ይገባቸዋል፤ (ኤፌ.6:4)። ሆኖም ይህ ማለት ክርስትና በዘር ይተላለፋል ማለት አይደለም። የአማኝ ልጅ ራሱ ጌታን በግሉ ካልተቀበለ የወላጆቹ እምነት አያድነውም፤ (ሕዝ.18:10-13)።

## ትምህርት 3

### የ3ኛ ቀን ጥናት

የንባብ ክፍል:- (1ኛቆሮንቶስ 7:17-24)

ማሳሰቢያ!

በዚህ የተሰጠውን ዝርዝር ጥናት ከመመልከትህ በፊት ቃሉን በራስህ በመመርመር ለቀረቡልህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሞክር።

ጥያቄ 15. በቁጥር 20 ላይ «እያንዳንዱ በተጠራበት መጠራት እንዲዚሁ ይኑር» ሲል ሐዋርያው ምን ማለቱ ነው?

ጥያቄ 16. ባሪያዎች በባርነታቸው እንዳይጨነቁበት ባሉበት ሁኔታ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ ከመከረቸው፤ በቁጥር 23 ላይ «የሰው ባሪያዎች አትሁኑ» ማለቱ ምን ማለቱ ነው?

በዚህ ክፍል ውስጥ ሐዋርያው ስለ ጋብቻ ተወት አድርጐ ስለ አጠቃለይ የክርስቲያን ኑሮ ይናገረል። በቁጥር 17 ላይ እያንዳንዱ ክርስቲያን ጌታን ሲቀበል በነበረው ኑሮ መቀጠል እንጂ ክርስቶስን ከተቀበለ በኋላ ኑሮውን ለመቀየር ክርስትና አያስገድደውም። መቀየር ያለበት የኃጢአት ኑሮን እንጂ የሥራ ስምሪትን መቀየር አስፈላጊ አይደለም። በማንኛውም ሥራ ብንሠማራ በዚያ ጌታን ማገልገል እንችላለን።

በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ ሰው ይሰማሪባቸው የነበሩትን አንዳንድ የሥራ መስኮች ምሳሌ ይሰጣል። እነርሱም ባርነትና ጌትነት ናቸው፤ (20-24)። «ባርያ ሆነህ ተጠርተህ እንደሆነ አይገደድህ»። ይህም ማለት ባርነት የክርስቶስ አገልጋይ ከመሆን አይከለክልህም ማለት ነው። ሆኖም ባርነትን የተመረጠ ኑሮ አድርገህ ተቀበለው ማለቱ አይደለም። ሰው በነጻነት ለመኖር መንገድ ካገኘ ነጻነትን ይጐናጸፍ፤ ነገር ግን ነጻነት መጐናጸፍ ባይችል ነጻ እስከሚሆን ድረስ በባርነቱ የክርስቶስ አገልጋይ መሆን ይችላል።

እንዲህ በባርነቱ በክርስቶስ የማይጸገፍ ሆኖ ነጻነት ስለሌለው ሁልጊዜ ተስፋ ቢስ በመሆን ቢኖር ለሰው ባሪያ መሆኑ የእግዚአብሔር ባሪያ ከመሆን ከልክሎታል ማለት ነው። ይህም ከሆነ የእግዚአብሔር ባሪያ መሆኑ ቀርቶ የሰው ባሪያ ሆነ ማለት ነው፤ «ባሪያ ሆኖ በጌታ የተጠራ የጌታ ነጻ ነውና፤» (ቁጥር 22)።

ችግር ሰውን እግዚአብሔርን ከማገልገል ሊከለክለው አይችልም። ምንም እንኳ ሰው ክፉ በሆነ ባርነት ቢያዝም በዚያ ውስጥ እንኳ በመንፈስ ነጻ የወጣ ነውና አገልግሎቱን ለእግዚአብሔር ሊያደርገው ይችላል።

ይህ የሐዋርያው ትምህርት «መጽሐፍ ቅዱስ ባርነትን ይደግፋል» ለሚለው ጥሬዝ ነጠቅ የነቀፋ አስተያየት መነሾ ሆኖአል። ነገር ግን እዚህ ላይ ሐዋርያው ነጻነትን አይቃወምም፤ «አርነት ልትወጣ ቢቻልህ ግን አርነትን ተቀበል፤» (ቁጥር 21)።

ሐዋርያው እዚህ ላይ ክርስቲያን በጭቆና ውስጥ ሳለ እንዴት ጭቆናን መቋቋም እንደሚችል መንፈሳዊ መምሪያ መስጠቱ ነው። በተጨማሪም ስለመገረዝና ስለአለመገረዝ ይናገራል፤ «ማንም ተገርዞ ሳለ ተጠርቶ እንደሆነ ወደ አለመገረዝ አይመለስ» (ቁጥር 18)። በሰው ልቡና ውስጥ ሁልጊዜ መጓጓት አለ። እግዚአብሔር በሰጠው ረክቶ በአእምሮ ሰላም እንደመቀመጥና እግዚአብሔርን እንደማገልገል ሁልጊዜ የሌላውን ነገር ወይም ያልሆነውን እያሰበ በማጉረምረም መኖር ለክርስቲያን አይገባውም። «እያንዳንዱ በተጠራበት እንዲሁ ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ ይኑር፤» (ቁጥር 24)። እንደዚህ ሆኖ በመንፈስ ነጻ ሆኖ በምስጋና ለመኖር ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ነጻነት ተሰጥቶታልና በሆነው ባልሆነው እያማረረ መበሳጨት የለበትም። ነገር ግን ክርስቲያን በተሰጠው የኑሮ ጥሪ በእግዚአብሔር ፊት በምስጋናና በጽል መኖር አለበት።

ጥያቄ 17. ይህን ምክር በትምህርታቸው፥ በዘራቸው፥ በኑሮ ደረጃቸው፥ ወዘተ ለማይደሰቱ ሰዎች እንዴት አድርገን ነው እንዲገባቸው ማድረግ የምንችለው?

## ትምህርት 3

### የ4ኛ ቀን ጥናት

የንባብ ክፍል:- (1ኛቆሮ.7:25-35)

መግቢያ

ሐዋርያው በዚህ ክፍል ውስጥ አለማግባት ለምን ከማግባት እንደሚሻል ሁለት ምክንያቶችን በመስጠት ያስተምራል። እነዚህ ምክንያቶች:- 1ኛ/ በአሁኑ ዘመን ስደት ስላለ በጋብቻ ውስጥ ያሉ በስደት ጊዜ ካላገቡት የበለጠ

ስጸቱ ይከብጸቸዋል፤ (ቁጥር 28)፡፡ 2ኛ/ ጌታን በአንድ ልብ ለማገልገል አለማግባት ከማግባት ይሻላል፤ (ቁጥር 32-33)፡፡ ሆኖም ግን አለማግባት ሪስን የመግዛት ጸጋ ለተሰጣቸው ብቻ እንጂ ለሁሉ አይሆንም፡፡ ይህ ጸጋ ያልተሰጣቸው ባያገቡ ሐዋርያው እንዳለው በስሜት ወደ መቃጠል ይወድቃሉ፡፡ እንደዚያ እንዳይሆን ካለማግባት ማግባት ይሻላል፤ (7፡1-2)፡፡

ጥያቄ 18. በቁጥር 25 ላይ «የጌታ ትእዛዝ የለኝም» ሲል ምን ማለቱ ነው?

ጥያቄ 19. በቁጥር 28 ላይ «እንዲህ በሚያደርጉ ላይ በሥጋቸው መከራ ይበዛባቸዋል» ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አብራራ፡፡

ጥያቄ 20. አለማግባት ከማግባት የተሻለ መሆኑን በሁለት ምክንያቶች ይጸገፋል፤ እነዚህን ምክንያቶች ጥቀስ፤ (ቁጥር 29-35)፡፡

ቁጥር 25 «ስለደናግልም የጌታ ትእዛዝ የለኝም» እንደበፊተኛው (ቁጥር 10 እና 11 ጌታ ያስተማረው በወንጌል እንደተጠቀሰው የለኝም ማለቱ ነው እንጂ መንፈስ ቅዱስ ይህንን እንዲናገር አልመራውም ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም በቁጥር 40 ላይ ይህን ሲያስተምር የእግዚአብሔር መንፈስ እየመራው እንደሆነ ይናገራል፡፡

«ምክር እመክራለሁ»፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የሚያስተምራቸው እንደ ትእዛዝ ሳይሆኑ በምርጫ የሚደረጉ ምክሮች ናቸው፡፡ ሰው የሚወስደውን የእርምጃውን ውጤት አውቆ ባለው ነፃነት እንዲወስን ሐዋርያው ስለደናግል ጋብቻ ምክር ይሰጣል፡፡ የማግባትንም ያለማግባትንም ውጤት በየመሥመሩ በማስቀመጥ ውሣኔው የምእመኑ እንደሆነ ያስተምራል፡፡ በተጨማሪ ይህ ትምህርት ምእመኑን «ምነው ባላገባሁ ኖሮ» ወይም ያላገባው «ምነው ባገባሁ» እያለ ያለበትን ሁኔታ እንዳያማርር ይመክራል፤ (ቁጥር 27)፡፡

ማግባት ወይም አለማግባት የግል ምርጫ ጉዳይ ወይም ለእያንዳንዱ እግዚአብሔር እንደሰጠው በነፃነት የሚወሰድ እርምጃ ነው እንጂ የኃጢአትና የጽድቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ማግባትም አለማግባትም ተፈቅዷል፤ (ቁጥር 28)፡፡ እንዲያውም ጋብቻን መከልከል የዲያብሎስ ትምህርት እንደሆነ ሐዋርያው በሌላ ቦታ ያወግዛል፤ (1ኛጢሞ.4፡1 እና 2)፡፡

ጥያቄ 21. ለምንድነው አንዳንድ የክርስቲያን ሃይማኖት ቡድኖች መሪዎቻቸው (ቄሶቹ) እንዲያገቡ የሚፈቅዱላቸው? ጠይቃቸውና ምክንያታቸውን ግለጽ፡፡

ከቁጥር 29-31፡- በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ያለው ምክር በቁጥር 27 ካለው ምክር ጋር ይስማማል፡፡ ሰው በማግባቱ «ምነው ባላገባሁ ኖሮ» ወይም ባለማግባቱ «ምነው ባገባሁ» ብሎ መጸጸትና የልብ ሰላም

ማጣት የለበትም:: ምክንያቱም ጋብቻ የዚህ ዓለም ኑሮ ጉዳይ ብቻ ስለሆነ አንድ ቀን እንዳልነበር የሚሆንበት ወቅት ይመጣል:: ጋብቻ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የአሁኑ ሥርዓት የሚሻርበት ወቅት ስለሚመጣ ክርስቲያን ባለው ተደስቶ በምስጋናና ረስን በመግዛት መኖር አለበት:: ከዚህ ሃሳብ ጋር የዮሐንስ ራእይ 21:4ን ተመልከት::

ነገር ግን በጊዜው ችግር ምክንያት አለማግባት ይቀላል በማለት ሐዋርያው የራሱን ምክር ከርህሩኄ አንዓር ይሰጣል፤ (ቁጥር 25 እና 32-35):: ሰው ካገባ ለራሱ ማሰብ ቀርቶ ለሚስቱና ለልጆቹ መጨነቅ ይጀምራል:: ይህም በችግር ላይ ችግር ያስከትላል:: ስለዚህ ሙሉ ልቡን በጌታ አገልግሎት ላይ ማሰማራት ያስቸግረዋል:: እንግዲያስ ሰው ከጋብቻ የሚቆጠበው ለራሱ ምቾትን ፍለጋ ሳይሆን ባልተከፋፈለ አእምሮ ጌታን ማገልገል እንዲችል መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: ሐዋርያው የራሱን ሕይወት ምሳሌ በማድረግ ሰው ባለማግባት ምን ያህል ለጌታ ሥራ በነፃነት እንደሚሰማራ ይናገራል:: ስለዚህ ከማግባት ይልቅ አለማግባትን ይመርጣል::

ጥያቄ 22. ያላገባ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲኖር ብዙ ሰዎች እንዲያገባ ሊያስገድዱ የሚሞክሩት ከምን የተነሣ ነው? ይህ ትክክል ነው?

አሁንም ደግመን መገንዘብ ያለብን:- 1ኛ/ ጋብቻ ኃጢአት የለበትም:: 2ኛ/ አለማግባት የግል ጥቅምን ፍለጋ መሆን የለበትም፤ ግን ለጌታ ሕይወትን የመሠዋት ጉዳይ ነው እንጂ፤ ማቴ.19:12ን እንመልከት:: «ስለመንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ::» ይህም ማለት ራሳቸውን እንደ ስልብ ቆጥረው በነጠላ ኑሮ ጌታን የሚያገለግሉ ማለት ነው:: «ያልተጋባች ሴትና ድንግል በሥጋም በነፍስም እንዲቀደሱ የጌታን ነገር ያስባሉ፤ የተጋባች ግን ባሏን እንዴት ደስ እንድታሰኘው የዓለምን ነገር ታስባለች፤» (ቁጥር 34)::

ነገር ግን ይህን የመሥዋዕትነት ኑሮ መቀበል የሚችሉ ረስን መግዛት የተሰጣቸው ብቻ ናቸው እንጂ ሁሉም አይደሉም:: ስለዚህ ሐዋርያው «ላጠምዳችሁ ብዬ አይደለም» ይላል:: «የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች» ወይም «አተርፍ ባይ አጉዳይ» እንዳንሆን መጠንቀቅና በአቅማችን ማደር ይኖርብናል::

## ትምህርት 3

### የ5ኛ ቀን ጥናት

በዚህ ሳምንት ጥናት ላይ ክለሳ አድርገህ የመወያያ ጥያቄዎችንም

በጥናት መልክ ሠርተህ ከጨረስክ በኋላ ሬስህን ለሳምንታዊው ስብሰባ አዘጋጅ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ፦ ከተማሪዎቹ ጋር ሊካፈለው የሚችል በዚህ ሳምንት የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚገኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወይም ሃሳብ በመምረጥ የስብሰባው መሪ ከ5 እስከ 10 ደቂቃ ያህል ጊዜ የሚወስድ የስብከት ጊዜ ማዘጋጀት አለበት።

2. ጸሎት፦ አብረቻሁ ለ10 ደቂቃ ያህል ስለእያንዳንዳቸሁና ስለ ቤተ ክርስቲያን ችግር ጸልዩ።

3. ክለሳ፦ ለ15 ደቂቃ ያህል የዚህን ሳምንት ትምህርት ጠቅለል ባለ መልኩ ተመልከቱት (ክለሳ አድርጉ)።

መምህር፦ እያንዳንዱ ተማሪ ሳምንታዊ ትምህርቱን ማጠናቀቁንና በጸንብ መረዳቱን ይዩ። እያንዳንዱ ተማሪ ከትምህርቱ የተማረውን ነገር በዝርዝር ይጻፍ።

የስብሰባው መሪ፦ በዚህ ሳምንት የትምህርት ክፍል ላይ የተመሠረተ ትንሽ ፈተና ብትሰጣቸው ይመረጣል።

4. ውይይት፦ ለ25 ደቂቃ ያህል የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው። ሁሉም ሰው የራሱን ሃሳብ ማካፈሉን እርግጠኛ ሁን። የእነዚህን ጥያቄዎች ተግባራዊነት በማሳየት ተማሪዎቹ ሰፋ ያለ አመለካከት እንዲኖራቸው አድርግ።

1ኛ/ ሀ. በ6:12-20 ዝሙትን የከለከለበትን ምክንያቶች ዘርዝር።
ለ. በቤተ ክርስቲያንህ የዝሙት ችግር አለ?
ሐ. ምን ዓይነት እርምጃ እየወሰዱ ናቸው?

2ኛ/ ሀ. አለማግባት የተፈቀደው ለነማን ብቻ ነው?
ለ. እነዚህን እንዴት ለይተን ማወቅ እንችላለን?
ሐ. ለምንስ አለማግባት የተሻለ ነው ተባለ?
መ. እነዚህ ምክንያቶች ላለንበት ዘመን ጠቀሜታቸው ምንድነው?

3ኛ/ ሀ. የአማኝ ልጆች ቅዱስ ናቸው ሲል ምን ማለቱ ነው?
ለ. የግል እምነታቸው የት ይገባል?
ሐ. የአማኝ ልጆች የበለጠ በእግዚአብሔር መንገድ እንዲሄዱ ወላጆቻቸውና ቤተ ክርስቲያናቸው ያለባቸው ኃላፊነት ምን ዓይነት ነው?

5. ጸሎት፦ የተማረቻሁትን ነገር ተግባራዊ እንድታደርጉት

የእግዚአብሔርን እርዳታ በጸሎት በመጠየቅ ስብሰባችሁን ዝጉ።

## የሳምንቱ አጠቃላይ መግቢያ

በዚህ ሳምንት ከምዕራፍ 7:38-40 ጀምረን እስከ ምዕራፍ 9:14 እናጠናለን። በ7:38-40 ያለው ስለ ጋብቻ የመደምደሚያ ሃሳብ ነው። ምዕራፍ 8 ላይ ሐዋርያው አዲስ ሃሳብ ይጀምራል፤ ያም ስለ ክርስቲያን ነፃነት ነው። ይህንን ሃሳብ እስከ ምዕራፍ 10 መጨረሻ ድረስ ይከታተለዋል። ምዕራፍ 10ን በሚቀጥለው ሳምንት እናጠናለን።

እንግዲህ በዚህ ክፍል ሐዋርያው የክርስቲያንን ነፃነትና የፍቅርን ግዴታ በማወዳደር ይጽፋል። ሌሎችን ለመጥቀም ሲል ክርስቲያን በክርስቶስ ያለውን ነፃነት በፍቅር መሻር አለበት። እንግዲህ እኛም ይህ ቃል እንዴት እንደሚመለከተን እያሰብን የሳምንቱን ጥናት እንጀምር።

## ትምህርት 4

### የ1ኛ ቀን ጥናት

የንባብ ክፍል:- (1ኛቆሮ.7:36-40)

ጥያቄ 1. ድንግመና ለማግባት የሚፈቀደው መቼ ነው? (ቁጥር 39ና 40፤ 1ኛቆሮ.7:15፤ ማቴ.5:32)

ቁጥር 36 የተለያየ ትርጉም የተሰጠው ከባድ ጥቅስ ነው። በዚህ ላይ ባደረግሁት ጥናት መሠረት የሚመስለኝን ትርጉም አቀርባለሁ፤ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ አጥጋቢ የሆነ ትርጉም አላገኘሁም።

አሁን ያለውን የአማርኛውን ትርጉም ቃል በቃል ከግሪኩ ከተተረጐመው ጋር እናስተያየው። ከግሪኩ ቃል በቃል ሲተረጐም እንዲህ ይላል:-

— ነገር ግን ሰው የእርሱ ስለሆነችው ድንግል የማይገባውን እንዳደረገ ቢያስብ፥ ድንግሊቱም በዕድሜ እየገፋች ብትሄድ፥ እንዲሁም ለማድረግ ግዴታ ቢኖርበት፥ የሚወደውን ያድርግ፤ ኃጢአትን አይሠራም ይጋቡ።

እንግዲህ በዚህ መሠረት ሁለት አተረጓጐሞች ይገኛሉ፤ አንደኛው የተጠቀሰው ሰው የድንግሊቱ አባት ሲሆን ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ የተጠቀሰው ሰው የድንግሊቱ እጮኛ ነው። አባቷ ነው የሚሉ ይጋቡ የሚለው ግሥ መተርጐም ያለበት «ያጋባቸው» ብሎ ነው ይላሉ።

የሁለተኛውን አተረጓጐም የሚደግፉ ደግሞ እንዲህ ይላሉ፤ ምንም እንኳ ገሡ ያጋባቸው የሚል ትርጉም ቢኖረውም በዚህ ጥቅስ ላይ ተስማሚው አተረጓጐም ይጋቡ የሚለው ነው ይላሉ። በተጨማሪም በነጠላ ቁጥር ሆኖ ያጋባቸው ሳይሆን ግሡ በብዙ ቁጥር የተነገረ ስለሆነ «ይጋቡ» ተብሎ መተርጐም አለበት፤ ያም እጮኛሞቹን ነው የሚያመለክተው ይላሉ።

የመጀመሪያው አተረጓጐም ይመረጣል፤ የሚከተሉትም ምክንያቶች ይህንኑ ያረጋግጣሉ።

1ኛ/ ለወጣቶቹ በእጮኝነት መዋዋል በዚያን ጊዜ ባህላቸው አይፈቅድም፤ ነገር ግን አባት ድንግል ሴት ልጁን በጋብቻ መስጠት የተለመደ ነበር። ስለዚህ የጥቅሱ ሃሳብ ይህ ነው፤ «አንድ አባት ሴት ልጁን ለጋብቻ ባለመስጠቱ የማይገባውን እንዳደረገ ቢመስለው ያጋባት»።

2ኛ/ በግሪክ ቋንቋ «የእርሱ የሆነችው ድንግሊት» የሚለው አነጋገር ለእጮኛ አይውልም፤ ለአባት ግን ይውላል።

3ኛ/ እጮኛ ብትሆን ኖሮ እጮኛዋ ላለማግባት ከወሰነ ለምን እንደ በደል ይቆጠረል? የማይገባስ ለምን ይሆናል? አላገባም ብሎ ከተዋት አሁን የርሱ አይደለችም። አባት ከሆነ ግን ጋብቻን ከከለከላት «ይህችን ልጅ በደልኳት» ብሎ ትክክለኛ ነገር ማድረግ አለማድረጉ ሊያጠራጥረው ይችላል።

ስለዚህ የጥቅሱ ጠቅላላ አነጋገር ይህ ነው፤ አንድ አባት ወጣት ልጃገረድ ልጅ ኖረው እንዳታገባ አስጠብቋት የማግቢያ ወቅቷ ሲተላለፍባት አይቶ የማይገባውን ያደረገ ቢመስለውና እንዲያጋባት ግድ ቢሆንበት ለጋብቻ ቢሰጣት ኃጢአት አያደርግም፤ የቀረበላት እጮኛና እርሷ ይጋቡ።

ቁጥር 37:- አሁንም የግሪኩን ቃል በቃል መተርጐም አለብን፤ የአማርኛ ትርጉማችን በቂ አይደለም። ግን በሩሱ ልብ ጸንቶ የቆመ፥ ግዴታ ከሌለበትና፥ በሩሱ የመወሰን መብት ካለው፥ የሩሱም የሆነችውን ድንግል በድንግልና ለመጠበቅ በሩሱ ልብ ወስኖ ከሆነ መልካም አደረገ።

እንግዲህ የጥቅሱ ሃሳብ፥ ይህ አባት ልጃገረድ ልጁን በድንግልና እንድትኖር በሩሱ ሳይጠራጠር የወሰነና ይህን ለመወሰን መብት ካለው (የሰው ተገዥ ባሪያ ካልሆነ ወይም አንድ ዓይነት ግዳጅ ከሌለበት ማለት ውል መሳይ ነገር ባያስገድደው) መልካም አደረገ።

ቁጥር 38:- ይህ ቁጥር ቃል በቃል ከግሪኩ ሲተረጐም ይህን ይመስላል፤ እንዲሁም ድንግሊቱን በጋብቻ የሰጠ መልካም አደረገ፤ በጋብቻ ያልሰጣትም የተሻለ አደረገ።

ቁጥር 39 እና 40:- ሰው ዳግመኛ ማግባት የተፈቀደለት ሚስቱ ከሞተች ነው። የጳውሎስ ምክር ግን ያው ከላይ በተዘረዘረው ምክንያት ሳታገባ ብትኖር የተሻለ መሆኑን ይናገራል።

በ1ኛ ቆሮ.7:15 ላይ ደግሞ የማታምነው ከተለየች አማኙ በጋብቻው ያልታሰረ መሆኑን ስለገለጠ እንግዲያስ ደግመኛ ለማግባትም ተፈቅዷል ማለት ነው። ባሏን ትታ እንደሄደችው አማኝ (ቁጥር 10ና 11) በጋብቻው ስላልታሰረ ሳያገባ እንዲኖር ግዴታ የለበትም፤ «ወንድም ቢሆን ወይም እህት እንዲህ በሚመስል ነገር አይገዙም»። ስለዚህ የማታምን ሚስቱ ጥላው ከሄደች ደግመኛ የማግባት መብት ስላለው ይህ ደግመኛ ለማግባት ሁለተኛው የተፈቀደ መንገድ ነው። ይህ መደረግ ያለበት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አይተውት አማኙ በደለኛ አለመሆኑን ቤተ ክርስቲያን ስትመሰክር ብቻ እንጂ በግል መደረግ የለበትም። እንደዚህ ከሆነ አማኝ ሚስቱን በግፍ ሊበድላት እንደሚችል መጠረጠር የለብንም።

ጋብቻ ፈርሶ ሌላ ማግባት የሚፈቀድበት ሌላ አንድ ተጨማሪ ምክንያት አለ፤ ያም ዝሙት ነው። ማቴ.5:32 እና 19:9። ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ማግባት ስለተከለከለ፤ እንግዲያስ በዝሙት ምክንያት ሚስትን ፈትቶ ሌላ ማግባት ተፈቅዷል ማለት ነው። በዚህም መንገድ ሰው በግሉ ሳይሆን ነገሩ በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ተጠንቶ መረጋገጥ አለበት። ሚስቴ አመንዝራለች ወይም ባሌ አመንዝሮአል በማለት ጋብቻን በግል ማፍረስ ከጌታ ሥርዓት ውጭ መሆን ስለሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ዝሙት መፈጸሙ እንኳ በረጋገጥም በንስሐና በይቅርታ ጋብቻ እንዲጸና ለማድረግ ከፍቸው በፊት ጥብቅ ሙከራ መደረግ አለበት።

ጥያቄ 2. ያንተ ቤተ ክርስቲያን ስለ ፍቺና ስለ ጋብቻ የምታስተምረው ምንድን ነው?
- እንዴት ነው ከዚህ ትርጓሜ ጋር የሚመሳሰለው?
- የሚለያየውስ እንዴት ነው?

## ትምህርት 4

## የ2ኛ ቀን ጥናት

(ምዕራፍ 8:1-6)

### ክፍል 5:- ጣዖትና ነፃነት፤ ከምዕራፍ 8 እስከ ምዕራፍ 10 አጠቃላይ መግቢያ

በመጀመሪያው መቶ ዓመት ይኖሩ ለነበሩ ክርስቲያኖች የጣዖት ጉዳይ ከባድ ችግር ያስከተለ ነበር። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሐዋርያውን ከጠየቁት ጥያቄዎች አንዱ ስለ ጣዖት ነበር። ስለ ጋብቻ ለጠየቁት ጥያቄ በቂ መልስ ከሰጠ በኋላ አሁን ወደ ሁለተኛው ጥያቄያቸው ዘወር ይላል።

ለእነዚህ ክርስቲያኖች ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ በሁለት መንገድ ችግር አስከትሎባቸው ነበር። አንደኛው በየሄዱበት ግብዣ ያጋጥማቸዋል። ይህንንም ግብዣ የሕብረተሰቡ አባል የሆነ ሁሉ መካፈል ነበረበት። ካልተካፈሉ ከሕብረተሰቡ ጋር ከባድ የቅያሜ ግጭት ይደርስባቸው ነበር።

ሁለተኛው ችግር በሥጋ ገበያ ሄደው የሚገዙት ሥጋ አስቀድሞ ለጣዖት የተሠዋ ነበር። እንደልማዳቸው የሕብረተሰቡ አባሎች ለጣዖት ከሠዉ በኋላ ሲሠዉ ሊሰገዱ ለመጡት ይታደላል፤ ሲሠዉ ለካህኑ ይሰጣል። ካህኑ የተሰጠውን ስለማይጨርሰው የተረፈውን በገበያ አውጥቶ ይሸጣል። እንግዲህ በገበያ ያለው ሥጋ አስቀድሞ ለጣዖት ተሠውቶ ነበር ማለት ነው።

ለዚህ ችግራቸው መፍትሄ እንዲነግረቸው ሐዋርያውን ይጠይቁታል። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ያለው ውይይት ይህን ጥያቄ በመመርኮዝ ነበር።

1ኛ ቆሮ.8:1-6ን ካነበብህ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 3. በቁጥር 1 ላይ አለን የሚለው እውቀት ምን ዓይነት እውቀት ነው?
ጥያቄ 4. ጣዖት ከንቱ ከሆነ ለጣዖት የተሠዋ ሥጋስ?
ጥያቄ 5. በቁጥር 6 ላይ እንደተጠቀሰው በአብና በወልድ መካከል ያለውን ዝምድና ሰፋ ባለ አነጋገር ግለጽ።

ቁጥር 1:- ለጣዖት ስለተሠዋ ሥጋ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እውቀት ያላቸው መሆኑን ገልጸውለት ባላቸውም እውቀት የተመኩ ይመስላል። «ለጣዖት ስለተሠዋ ሥጋ ሁላችን እውቀት አለን» በማለት ስለዚህ ነገር እውቀት ያላቸው እነርሱ ብቻ እንዳልሆኑም ይገልጽላቸዋል። ይህ እውቀት ምን እንደሆነ ዝቅ ብሎ ይዘረዝረል፤ (ቁጥር 4)።

አለን የተባለው የእውቀት ፍሬ ነገር ይህ ነው፤ አንድ አምላክ ብቻ ስላለ ጣዖት አምላክ አይደለም፤ እንዲሁ ከንቱ ነገር ነው። ከንቱ ነገርም ስለሆነ ሰው በዚህ ነገር መጨነቅ አይገባውም። ስለዚህ ሰው ለከንቱ ነገር የተሠዋውን ቢበላ ምንም ጉዳት የለበትም እያሉ ነገሩን ይህን በመሰለ ግምገማ ውስጥ አስቀምጠውት ነበር።

ቁጥር 2:- ሆኖም በዚህ ግምገማቸው ላይ የዘነጉት ነገር እንዳለ ያስረዳቸዋል። ያም የዘነጉት ነገር ፍቅር ነው። «እውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንጻል»። ይህም ማለት ሰው እውቀት አለኝ ብሎ እውቀቱ የመረውን ነገር ሁሉ ማድረግ አይገባውም። ያ የሚወስደው እርምጃ በሌሎች ላይ ምን ያስከትላል ብሎ ማመዛዘን ይኖርበታል። ካላመዛዘነ ግን በእውቀቱ ትዕቢት አድርበታል፤ ሥራውም ቤተ ክርስቲያንን የሚገነባ ሳይሆን የሚያፈርሳት ሆኖ ይገኛል።

ቤተ ክርስቲያንን በማይገነባትና በሚያፈርሳት ሥራ መሠማራት አጸፃፍ እንደሆነ ሐዋርያው ቀደም ሲል ተናግሮአልI (1ኛ ቆር.3:17)። ነገር ግን ሰው በእውቀት ታብዮ ሳይሆን በፍቅር ተመርቶ ቢፈጽ ቤተ ክርስቲያንን ይገነባልI «ፍቅር ግን ያንፃል።»

ከዚህም በላይ ምንም እንኳ ሰው ብዙ እውቀት ያለው ቢሆንም ሊታወቅ የሚገባውን ገና አላወቀምI ሊያውቅም አይችልም። ስለዚህ የሰው እውቀት ሁልጊዜ ጎደሎ ስለሆነ በእውቀቱ ላይ መደገፍ የለበትም። የቆሮንቶስም ሰዎች ያላቸው እውቀት በቂ አለመሆኑን ተገንዝበው በትህትናና በፍቅር መፈፀድ ይኖርባቸዋል። ትህትናና ፍቅር የሌለበት እውቀት ምንጩ ከዲያብሎስ እንጂ ከእግዚአብሔር አይደለምና እውቀትን እንዴት እንደምንጠቀምበት ጥንቃቄ እናድርግI (ያዕ.3:15)።

ጥያቄ 6. የዛሬ ዘመን አማኞች በፍቅር ሳይሆን በእውቀት ብቻ ሲሠሩ የምናየው እንዴት ነው? በምሳሌ ገለጽ።

ቁጥር 3:- የፍቅር መጀመሪያው እግዚአብሔርን ማፍቀር ነው። እግዚአብሔርን ከመውደድ አንፃር እግዚአብሔር የወደዳቸውንም መውደድ እንችላለንI (1ኛ ዮሐ.4:20 እና 21)። የእውቀትም ጉዳይ በእግዚአብሔር መታወቅ ነው። ስለዚህ ሰው ስለ ራሱ ደስ መሰኘት ከወደደ በእግዚአብሔር በመታወቁ ብቻ ሊደሰት ይገባዋልI (ሉቃ.10: 20-22)።

በእግዚአብሔር መታወቅ ማለት ምን ማለት ነው? ከላይ ከሉቃስ ወንጌል እንደተገኘነው እያንዳንዱ ክርስቲያን ስሙ በእግዚአብሔር መዝገብ ስለሰፈረ በእግዚአብሔር ታውቋል። ይህም እውቀት የሚንከባከብና የእኔ ነህ የሚል ፍቅር ነው። ቅዱስ ዳዊት ስለዚህ እውቀት ሲጽፍ እንዲህ ይላልI «እግዚአብሔር የጻድቃንን መንገድ ያውቃልI የኃጢአን መንገድ ግን ትጠፋለችI» (መዝ.22:(23):6)።

ቁጥር 4:- ስለ ጣዖት አለን የተባለውን እውቀት ይጠቅሳል። ጣዖት ከንቱ እንደሆነ እናውቃለን። ከአንዱ አምላክ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።

ቁጥር 5-6:- ምንም እንኳ ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን አምላክና ጌታ አድርገው ቢሰግዱላቸውና ቢያገለግሏቸውም እኛ ግን አንድ አምላክ ብቻ እንዳለን እናውቃለን። ሌሎቹ ግን ከንቱ ነገሮች ብቻ ናቸው።

ጥያቄ 7. በዛሬ ዘመን አንዳንድ ሰዎች ከእግዚአብሔር ሌላ አምላክ የሚያደርጉት ነገር ምንድነው?

ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን። ሁሉ ነገር ከአብ የመነጨ ነው። ከዚያም ቀጥሎ «ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን»። በማለት በአብና በወልድ መካከል ያለውን ዝምድና ይገልፃል። ሁሉ ነገር ከአብ ሲሆን÷ ሁሉ ነገር ደግሞ በወልድ በኩል (ወይም አማካይነት) ነው። ይህም ማለት እግዚአብሔር አብ ሥረውን ሁሉ (የመፍጠርንም የማዳንንም ሥራ) የሠረው በእግዚአብሔር ወልድ በኩል ነው ማለት ነው።

ጥያቄ 8. ይህንን እውነት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ነን ለሚሉት እንዴት እንድንመልሳቸው ልንጠቀምበት እንችላለን?

## ትምህርት 4

## የ3ኛ ቀን ጥናት

የንባብ ክፍል:- (1ኛቆሮ.8:7-13)

ጥያቄ 9. በቁጥር 7 ላይ በሁሉ ዘንድ አይገኝም የሚለው እውቀት ምን ዓይነት እውቀት ነው?

ጥያቄ 10. በቁጥር 9 ላይ የተጠቀሰው መብት ምንድነው?

ጥያቄ 11. በቁጥር 10 ላይ «ሕሊናው አይታነጽበትምን» ማለቱ ምን ማለቱ ነው?

ቁጥር 7:- «ይህ እውቀት በሁሉ ዘንድ የለም»። ጣዖት ከንቱ እንደሆነ ሁሉ ክርስቲያኖች አያውቁም። በቁጥር 1 ላይ «ሁላችን እናውቃለን» ካለው ጋር ይህ ንግግሩ ሊጋጭ አይገባም። በቁጥር 1 ላይ ይህ እውቀት በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መካከል ብቻ ሳይሆን በሁሉም አገር ክርስቲያኖች ዘንድ ይገኛል ማለቱ ሲሆን በቁጥር 7 ደግሞ ይህ እውቀት በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ባሉ በእያንዳንዳቸው ክርስቲያኖች ዘንድ አይገኝም ማለቱ ነው።

ጣዖት ከንቱ መሆኑን ስላልተገነዘቡና ጣዖትን ለብዙ ጊዜ ከማምለክ የተነሣ አእምሮአቸው በጣዖት አምልኮ አስተሳሰብ ስለተጠመደ በጣዖት ነገር በቀላሉ ይረከሳሉ። ጣዖት ከንቱ ነገር መሆኑን የተገነዘበ ሰው ለጣዖት የተሠዋውን ቢበላ ምንም አይሆንም። ግን ጣዖት አንድ ኃይል አለው የሚል ልማድ ያለው ሰው ለጣዖት ከተሰዋው ሥጋ ቢበላ ሕሊናው ይረከሳል።

የሕሊና መርከስ ማለት ለጣዖት የተሠዋውን በሚበላበት ጊዜ ለጣዖት

ኃይል መስጠት የለመደ ደካማ አእምሮ ስላለው የተከለከለ ጣዖትን ያመለከ መስሎት ሕሊናው ይወቅሰዋል። ይህ የሕሊና ወቀሳ የሕሊና መርከስ ይባላል። ይህ እግዚአብሔርን ያስቀይመዋል እያለ ግን ደፍሮ ያን ሥራ ቢፈጽም በእውነትም እግዚአብሔርን ያስቀይማል። የሕሊና መርከስ እንግዲህ «በእምነት ያልሆነ ሁሉ ኃጢአት ነው» ከሚለው አስተሳሰብ ጋር ይወረረሳልI (ሮሜ 14:20)።

ጥያቄ 12. በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ በአንድ ነገር ላይ ይህ ተፈቅዷልI ይህ አልተፈቀደም ብለው በሃሳብ የሚለያዩ ሰዎች አሉን? ካሉስ የሚለያዩበት ሃሳብ ምንድነው? ጥያቄአቸው ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ይመሳሰላል ወይስ ይለያያል?

ቁጥር 8:- ጣዖት ከንቱ ስለሆነ ለጣዖት የተሠዋም በረሱ እንዲሁ ተራ ምግብ ከመሆን ሌላ ኃይል የለውም። ምግብም በሃይማኖት በኩል በረሱ ምንም ዋጋ የለውም። ሰው በመብል ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብም ከእግዚአብሔር ሊርቅም አይችልም። «ብንበላም ባንበላም ምንም አይተርፈንም»።

ቁጥር 9:- ስለምንበላው «ይህ እግዚአብሔርን ያስቀይም ይሆን» እያሉ አለመጨነቅ ትልቅ የክርስቲያን ነፃነት ነው። ነገር ግን እውቀት የጎደላቸው ክርስቲያኖች ይህን ነፃነት ገና አልተገናጸፉም። በዚህም ምክንያት «ደካሞች» ተብለዋል። <u>እንግዲህ መብል በረሱ ጉዳትም ጥቅምም ከሌለው፥ በመብልም ምክንያት ወንድም የሚሰናከል ከሆነ አለመብላትን በመምረጥ ነፃነታችንን በፍቅር ማሰር አለብን</u>። ስለዚህ ማየት ያለብን ነፃነታችንን ብቻ ሳይሆን ያ ነፃነታችን በወንድማችን ላይ ሊያስከትል የሚችለውንም ጭምር መሆን አለበት። ይህም በእውቀት ሳይሆን በፍቅር መመላለስ ማለት ነው። «እውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንፃል።»

ቁጥር 10:- በዚህ ቁጥር ላይ አንድ እውቀት ያለው ክርስቲያን እውቀቱን ያለ ፍቅር ሥራ ላይ ካዋለው የሚያደርሰውን በደል ሐዋርያው ይዘረዝራል። አንድ ሰው «ጣዖት ከንቱ ነውI ስለዚህ ለጣዖትም የተሠዋ እንዲሁ ተራ ምግብ ስለሆነ ብበላው ምንም አይጎዳኝ» ብሎ በጣዖት ቤት ቁጭ ብሎ ለጣዖት የተሰዋውን ሥጋ ይበላል። ነገር ግን ይህ እውቀት የሌለው ደካማ አማኝ ደግሞ ይህን አይቶ «እይ ይኸው እከሌ እንኳ በጣዖት ገበታ ይሳተፋልI ስለዚህ እኔም ልሳተፍ» ይልና ይሳተፋል። በቂ እውቀትም ስለሌለው «እዩ ከጣዖት ማዕድ በመካፈሌ አምላክን አስቀየምሁ» እያለ የሕሊና ክስ ያስጨንቀዋል። ግን ደግሞ መልሶ «እይ ገጽየለም እከሌስ በልቶ የለም?» እያለ በረሱ እምነት ሳይሆን ሰውን ብቻ በማየት በአምላኩ ፊት ይደፍረል። ይህ እንደዚህ ሕሊናውን መጣሱ እየተደጋገመ ሲመጣ ወደ ሌላም ኃጢአት በመንሸራተት በእምነቱ ይሰናከላል። ለዚህ ሁሉ

መነሻና የመሰናከያ አለት የሆነበት ን ያለፍቅር በእውቀቱ የተመካው ክርስቲያን ወንድም ነው።

«ሕሊናው አይታነጽበትምን?» ማለት ይህን ለጣዖት የተሠዋ ምግብ በእውቀት ሳይሆን በአምልኮት ለመብላት ይደፍረል ወይም ያን ለማድረግ ይገነባል ማለት ነው። የማይገባውን እርምጃ በድፍረትና በድንቁርና ይወስዳል። ይህን ለማለት «ገነባ» የሚለው ቃል ተመረጭ አይደለም። ይህን ቃል ሐዋርያው የተጠቀመው ምናልባት በአሽሙር መልክ ሳይሆን አይቀርም። ምናልባት የቆሮንቶስ አማኞች ጸካዎችን በእውቀት በመገንባት ሳይሆን በእርምጃ ለመገንባት ይሞክሩና የተባለውን ጉዳት በወንድማቸው ላይ አድርሰው ይሆናል። ስለዚህ ሐዋርያው በአሽሙር አነጋገር «አዎ እንዲህ ወንድምህን እያሰናከልህ ትገነባዋለህ!» ማለቱ ይሆናል።

ቁጥር 11-12:- ፍቅር በሌለው እውቀት ሰው እንዲህ ወንድሙን ሊጐዳ ይችላል። ይህም ወንድም ክርስቶስ የሞተለት ስለሆነ ይህን በደል ያደረሰው ሰው ሰውን ብቻ ሳይሆን ክርስቶስንም እንደበደለ ይታያል። ስለዚህ ሰው እርምጃውን በእውቀት ሚዛን ላይ ብቻ ሳይሆን በፍቅር ሚዛንም ላይ ማስቀመጥ አለበት። ፍቅርም ለሰው ብቻ ሳይሆን ለክርስቶስም የተሰነዘረ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ጥያቄ 13. በዚህ ዘመን በእውቀታችን ብቻ ሳይሆን በፍቅር ሚዛን ላይ መታየት ያለባቸው ነገሮች ምን ዓይነት ናቸው?

በዚህ ክፍል ውስጥ «ይጠፋል» የሚለው ቃል በግሪኩ የወደፊት ግሥ ሳይሆን የአሁን ግሥ ነው። ስለዚህ ጥፋቱ በዘላለም ኩነኔ ሳይሆን በአሁኑ ዘመን የሚደርስበትን ጉዳት ነው የሚያመለክተው። መጥፋት ማለትም በእምነቱ ተሰነካክሎ የክርስትና ሕይወቱ ይበላሻል ማለቱ ነው እንጂ የዘላለም ኩነኔ ይደርስበታል ማለቱ አይደለም። ሐዋርያው አንድ ክርስቲያን ከዳነ በኋላ የማይጠፋ የደህንነት ዋስትና እንዳለው አስተምሮአልI (ፊልጵ.1:6)።

ቁጥር 13:- ሐዋርያው ክርስቲያኖች ማድረግ ያለባቸውን እርሱም ሊያደርግ የተዘጋጀ መሆኑን ያውጃል። «ወንድሜን እንዳላሰናክል» ማለት የወንድሙን ሕሊና እንዳያረክስ ማለቱ ነው።

እዚህ ላይ ማሰናከል የሚለውን ቃል «ማስቀየም» ወይም «ቅር ማሰኘት» ከሚለው ሃሳብ ጋር ማደባለቅ የለብንም። በወንጌል እምነት የሌሉ ሰዎች ክርስቲያኖች በሚያደርጓቸው አንዳንድ ነገሮች ቅር መሰኘታቸው ወይም መቀየማቸው አይቀርም። ለምን ዓርብና ሮብ ሥጋ ትበላላችሁ ብለው በመክሰስ በተሰጠን ነፃነት ቅር ሊሰኙብን ይችሉ ይሆናል። ግን በእነርሱ ቅሬታ የተነሣ ከክንቱ እምነታቸው መተባበር የለብንም። «አይ እሱ ዓርብ ሮብ ይጾማልI ስለዚህ ጾም እንደሚያጸድቅ ያምናል» የሚል የድንቁርና

እርምጃ ይወስዱም ይሆናል። ስለዚህ ቃሉን በጸንብ እንገነዘበው። 1ኛ/ «ወንድምህን» ነው የሚለው፤ 2ኛ/ ደካማን ወንድም ወደ ሕሊና ማርከስ እንምሬ ነው እንጂ የሚለው በወንጌል ብርሃን መረመድ በማይፈልጉ በጽንቁርናቸው ታሰሩ አይደለም የሚለው።

ጥያቄ 14. ላላመኑት የምናሳየው የሕይወታችን ምስክርነትና የደካማውን አማኝ ሕሊና መጠበቅ በምን ይመሳሰላል? በምንስ ይለያያል?

## ትምህርት 4

## የ4ኛ ቀን ጥናት

የንባብ ክፍል:- (1ኛ ቆሮ.9:1-14)

ጥያቄ 15. በቁጥር 1 ላይ «እኔ ነጻ አይደለሁምን?» ሲል ስለምን ዓይነት ነፃነት ነው የሚያወሪው?

ጥያቄ 16. በቁጥር 1 እና 2 በጥያቄ መልክ የሚያቀርባቸው የሐዋርያነቱ ማረጋገጫዎች ምን ምን ናቸው?

ጥያቄ 17. በቁጥር 5 የጌታ ወንድሞች የሚላቸው እነማን ናቸው? (ማር.6:3)

ጥያቄ 18. በቁጥር 9 ላይ «እግዚአብሔር ስለ በሬዎች ይገደዋልን?» የሚለውን ከማቴ.6:26 ጋር በማስተያየት አስታረቁ ሃሳብ ዓፍ።

ጥያቄ 19. ሐዋርያው በመብቱ ቢጠቀም ኖሮ የክርስቶስን ወንጌል ሊከለክል እንደሚችል በቁጥር 12 ላይ ይናገራል፤ ይህ መብት ምን ነበር? እንዴትስ ወንጌልን ይከለክል ነበር?

ስለ ክርስቲያን ነጻነት በምዕራፍ 8 ይናገር ነበር። ያንኑ ነጥብ ቀጥሎ በምዕራፍ 9 ያብራራዋል። ሌሎች ነፃነታቸውን በፍቅር ለወንድሞች ጥቅም መሰዋት አለባቸው ብሎ ካስተማረ በኋላ፥ የሚያስተምረውን በሥራ ላይ የሚያውል አስተማሪ መሆኑን ያረጋግጥላቸዋል።

ቁጥር 1-3:- በምዕራፍ 8 ላይ ጳውሎስ ምንም እንኳን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ቢሆንም በእውቀቱ ላይ ሳይሆን በፍቅር ላይ ተመሥርቶ እንደሚናገር ያሳየናል። በመጀመሪያ እርሱ ራሱ ነፃ የሆነ ሰው እንደሆነ ለቆሮንቶስ ሰዎች ያሳያቸዋል። ከሬለገ ሚስት የማግባትም ሆነ ለሐዋርያዊነት ሥራው ደመወዝ የመቀበል ነፃነት ነበረው። ነገር ግን ለወንጌል እንቅፋት ሳይፈጥር የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ሲል ነው ይህን ነፃነቱን ወደ ኋላ የተወው። በመጀመሪያ ግን ጳውሎስ አንዳንድ

ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሐዋርያነቱን አሳውቆ ነበር። 1ኛ/ «ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን አላየሁትምን?» ጌታን ያላየ ሐዋርያ መሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ሐዋርያነት በቤተ ክርስቲያን ሳይሆን በቀጥታ በክርስቶስ የሚሰጥ ሥልጣን ስለሆነ ነው፤ (ገላ.1:1 እና የሐዋ.9:10-18)። 2ኛ/ ይህ ሐዋርያነቱን እንዲሁ በአፍ ወሬ ሳይሆን በሥራ የተመሰከረለት ነበር። ይህም ራሳቸው የቆሮንቶስ ሰዎች በጳውሎስ አገልግሎት ወደ እምነት መምጣታቸው የጳውሎስን ሐዋርያነት ያረጋግጣሉ።

ቁጥር 4-7:- በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሐዋርያ ስለሆነ የሐዋርያነት መብት እንዳለው ይናገራል። «ልንበላና ልንጠጣ መብት የለንምን?» ይህ መብላትና መጠጣት በምዕራፍ 8 ላይ ያለው ዓይነት መብላትና መጠጣት ሳይሆን፥ ከታች ዝቅ ብሎ እንደዘረዘረው ደመወዝ ወይም አበል ማለቱ ነው።

እንደነጴጥሮስ ያሉት ሐዋርያትና የጌታ ወንድሞች ከቤተ ክርስቲያን ወጪ ሚስቶቻቸውን ይዘው ለወንጌል ሥራ የመዞር መብታቸውን ተጠቅመውበት ነበር። ባርናባስና ጳውሎስ ግን ምንም እንኳ ይህ መብት እንዳላቸው ቢገነዘቡም በመብታቸው አልተጠቀሙም። ራሳቸው በትርፍ ጊዜያቸው በሚሠሩት ነበር ይተዳደሩ የነበረው። ሥራን ትቶ ወንጌልን ብቻ መስበክ ለእነርሱም የተሰጠ መብት ነበር፤ ግን አልተጠቀሙበትም።

ከሕብረተሰቡ ልማድ ምሳሌዎችን በማቅረብ ነገሩን ያረጋግጥላቸዋል። እነዚህም የገበሬና የወታደር ምሳሌዎች ናቸው። ስለዚህ በወንጌል ሥራም የተሰማሩ ከወንጌል መተዳደሪያ መቀበል መብታቸው ነው። በወንጌል የሚገለገሉ ለአገልጋዮቻቸው ደመወዝ ሊከፍሏቸው የተገባ ነው።

«የጌታ ወንድሞች» የሚለው ማሪያም ከዮሴፍ የወለደቻቸው የጌታችን የሥጋ ወንድሞች ናቸው። ማርያም ከጌታችን በኋላ አልወለደችም የሚሉ ማስረጃ ይዘው ሳይሆን የሥጋ ግብር ርኩስ ነው ብለው ስለሚገምቱ ማርያምን ለማክበር አስበው ነው። ግን ይህ አስተሳሰብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይጋጫል። በምዕራፍ 7 ላይ ስንመለከት ሐዋርያው በአንድም ቦታ ከሚስት ጋር መተኛት ርኩስ ነው አላለም። አለማግባት ከማግባት ይሻላል ያለበትም ለአገልግሎት አመቺ እንዲሆን ነው እንጂ ከሚስት ጋር መተኛት ርኩስ ስለሆነ አልነበረም። እንዲያውም በዕብራውያን 13:4 ላይ ጋብቻ ክቡርና ንጹሕ እንደሆነ ይናገራል። እንዲሁም እግዚአብሔር የፈጠረው ስለሆነ በምስጋና መቀበል አለብን እንጂ ርኩስ ነው ማለት እግዚአብሔርን መስደብ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ጋብቻን ማረከስ የአጋንንት ትምህርት መሆኑንም ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞ.4:1-3 ላይ አስተምሮአል።

ከቁጥር 8-12:- የወንጌል አገልጋዮች በሚገለገሉት ምእመናን ሊረዱ ይገባቸዋል የሚለውን ሃሳብ በሰው ባህል ላይ ያም በገበሬና በወታደር ወግ

ላይ ብቻ አልመሠረተም። ከመጽሐፍ ቅዱስም ማስረጃ ያቀርባል። «የሚያበራየውን በሬ አፋን አትሰር» ብሎ ሙሴ እንዳዘዘና ይህ ስለሰዎች እንደሚናገር ያስረዳልⵊ (ዘዳ.25:4)።

«እግዚአብሔር ስለ በሬዎች ይገደዋልን? ይህን የሚለው ፈጽሞ ስለእኛ አይደለምን?» ይህ አነጋገር እግዚአብሔር ለበሬዎች አያስብም ማለት ሳይሆን አነጋገሩ እንዲህ ነው። «እግዚአብሔር ለበሬዎች አስቦ ይህን ዓይነት ሕግ ካወጣ እኛም ሰዎች ከእንስሳት ስለምንበልጥ እንንገዲያስ ሕጉ ከበሬዎች ይልቅ እኛን በበለጠ ይመለከተናል።» ይህን ከማቴ.6:25-30 ጋር አስተያይ።

ገበሬ የዘሬውን ዓይነት ዋጋ መቀበል ከቻለ የወንጌል አገልጋዮች መንፈሳዊ ነገር ዘርተው ሥጋዊ ጸመወዝ መቀበላቸው እንደትልቅ ነገር ሊገመት አይገባውም። ይኸውም ሲያንሳቸው ነውና እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ክብር በሚመጣውም ዓለም ያከብሬቸዋል።

ቁጥር 13 እና 14:- ይህን መብቱን ሐዋርያው አልተጠቀመበትም። ስለዚህ የቆሮንቶስም ክርስቲያኖች ለወንጽማቸው ሲሉ ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ የመብላት መብታቸውን መልቀቅ አለባቸው። ሐዋርያው የእርሱን መብት የለቀቀው «የክርስቶስ ወንጌል እንዳይከለከል» ስለሆነ እነርሱም ክርስቶስ ለሞተለት ወንድም ሲሉ መብታቸውን መልቀቅ መማር አለባቸው። ይህ የሚያስታብየው የእውቀትና የመብት እርምጃ ሳይሆን የፍቅር እርምጃ ነው።

በአምልኮት አገልግሎት የተሰማሩ ከቤተ መቅደስና ከመሠዊያው ለመካፈል መብት ያላቸው መሆኑን እንኳን ብሉይ ኪዳንን የሚያውቁ ቀርቶ በአህዛብ ወግ እንኳ የተጠበቀ ነበር። ይህንንም የቆሮንቶስ ሰዎች ጣዖት አምላኪዎች ስለነበሩ ያውቁታል። በአረመኔነታቸው ያከብሩት የነበረው አሁን ለክርስቶስ አገልጋዮች ሊነፈጋቸው አይገባም።

«የክርስቶስን ወንጌል እንዳንከለክል በሁሉ እንታገሣለን እንጂ በዚህ መብት አልተጠቀምንም።» ይህን ሲል ከቤተ ክርስቲያን ጸመወዝ ቢቀበል ኖሮ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ጸካሞች ከመሆናቸው የተነሣ «ጳውሎስ ወንጌልን የሚሰብከው ለጸመወዙ ሲል ነው» በሚለው በተቃዋሚዎች ነቀፋ ይሰናከሉ ነበር። ስለዚህ የተቃዋሚዎችን አፍ ለማዘጋትና በዚህም የወንጌልን እንቅፋት ለማስወገድ ሐዋርያው በመብቱ አልተጠቀመም ነበር። ይህን በሁሉም ቦታ አላደረገምⵊ ለምሳሌ ከፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች እርዳታ ይቀበል ነበር። ስለዚህ ጉዳይ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብⵊ 2ኛቆሮ.11:7-12።

ጥያቄ 20. ይህንን መብት በቤተ ክርስቲያንህ የሚጠቀሙበት እነማን ናቸው? የማይጠቀሙበትስ እነማን ናቸው? ለወንጌል ብለን

## ትምህርት 4

### የ5ኛ ቀን ጥናት

በዚህ ሳምንት ጥናት ላይ ክለሳ አድርገህ የመወያያ ጥያቄዎችንም በጥናት መልክ ሠርተህ ከጨረስክ በኋላ ራስህን ለሳምንታዊው ስብሰባ አዘጋጅ።

### ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ:- ከተማሪዎቹ ጋር ሊካፈለው የሚችል በዚህ ሳምንት የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚገኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወይም ሃሳብ በመምረጥ የስብሰባው መሪ ከ5 እስከ 10 ደቂቃ ያህል ጊዜ የሚወስድ የስብከት ጊዜ ማዘጋጀት አለበት።

2. ጸሎት:- አብረቻሁ ለ10 ደቂቃ ያህል ስለእያንዳንዳቸሁና ስለ ቤተ ክርስቲያን ችግር ጸልዩ።

3. ክለሳ:- ለ15 ደቂቃ ያህል የዚህን ሳምንት ትምህርት ጠቅለል ባለ መልኩ ተመልከቱት (ክለሳ አድርጉ)።

መምህር:- እያንዳንዱ ተማሪ ሳምንታዊ ትምህርቱን ማጠናቀቁንና በጸንብ መረዳቱን ይዩ። እያንዳንዱ ተማሪ ከትምህርቱ የተማረውን ነገር በዝርዝር ይጻፍ።

የስብሰባው መሪ:- በዚህ ሳምንት የትምህርት ክፍል ላይ የተመሠረተ ትንሽ ፈተና ብትሰጣቸው ይመረጣል።

4. ውይይት:- ለ25 ደቂቃ ያህል የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው። ሁሉም ሰው የራሱን ሃሳብ ማካፈሉን እርገጠኛ ሁን። የእነዚህን ጥያቄዎች ተግባራዊነት በማሳየት ተማሪዎቹ ሰፋ ያለ አመለካከት እንዲኖራቸው አድርግ።

1ኛ/ ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ የመፋታትና ደግመኛ የመጋባትን መመሪያ ዘርዝር። ለ. ቤተ ክርስቲያንህ እንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ሲገጥሟት እነዚህን መመሪያዎች እንዴት አድርጋ ነው የተጠቀመችባቸው?

2ኛ/ ሀ. 1ኛ ቆሮ.7:36-38ን ከትምህርቱ በመመልከት ትክክለኛውን

ትርጉም ስጥ።

ለ. ዛሬ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለው ሁኔታ በዚህ ምክር እንዴት መጠቀም ይቻላል?

3ኛ/ ሀ. በእውቀትና በፍቅር መካከል ያለውን ልዩነት አስረዳ።

ለ. ክርስቲያኖች በፍቅር ሳይሆን በእውቀታቸው ላይ የሚደገፉት በምን ዓይነት ሁኔታዎች ላይ ነው?

ሐ. ለጸካማ ክርስቲያኖች ስትል እውቀትህን ትተህ ነገሮችን በፍቅር ዓይን ተመልክተህ ያሳለፍክበት ወቅት ምን ዓይነት ነበር?

4ኛ/ ሀ. ሐዋርያው ስለ ራሱ ነፃነትን መሠዋት አጭር ሐተታ ፃፍ።

ለ. ልታደርጋቸው የምትችል÷ ነገር ግን ለወንጌል ስትል የተውካቸው ነገሮች ምንድናቸው?

ሐ. መብታችን ነው÷ ልናደርገው እንችላለን ብለን ካደረግነው በኋላ አንድ ነገር ለወንጌል እንቅፋት የሚሆነው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

መ. የዚህን ምዕራፍ ትምህርት የእስላምን ሥጋ ስለመብላት ወይም ስላለመብላት ላይ ተግባራዊ ለማድረግ እንሞክር።

- እዚህ ላይ እውቀትህ የሚጫወተው ሚና ምንድነው?
- ፍቅርስ የሚጫወተው ሚና ምንድነው?

5. <u>ጸሎት</u>:- የተማራችሁትን ነገር ተግባራዊ እንድታደርጉት የእግዚአብሔርን እርዳታ በጸሎት በመጠየቅ ስብሰባችሁን ዝጉ።

## አጠቃላይ የሳምንቱ ትምህርት መግቢያ

በዚህ ሣምንትም ባለፈው ሣምንት እናጠና የነበረውን ነው የምንቀጥለው። የሣምንቱም የጥናት ክፍል ከ9:15-10:13 ነው። በዚህ ክፍል ሐዋርያው ነፃነታችንን በፍቅር መሰዋት ለምን እንዳለብን ሁለት ተጨማሪ ምክንያቶች ይሰጠናል። እነርሱም 1ኛ. በትጋት የሮጡ ክርስቲያኖች በመጨረሻ ከእግዚአብሔር ሽልማት ስለሚቀበሉ ነፃነትን በፍቅር እየሰዋን መኖርን እንምረጥ፤ 2ኛ. ስለጣኦት ግድ የለሽ መሆን አደገኛ እንዳሆነ ከእስራኤላውያን ታሪክ እንማር የሚሉ ናቸው።